ኢፕድ
# አዲስ ዘመን
እሁድ 82ኛ ዓመት ቁጥር 001 መስከረም 1 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ


ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ


ሼህ ሱልጧን አማን ኤባ


ካርድናል ብርሃነኢየሱስ ሱራፌል


ቄስ ኪሮስ ሳቀው

# ኢትዮጵያውያን በአዲሱ ዓመት ለሰላም፣ እርቅና ሃገራዊ አንድነት ቅድሚያ ሰጥተው እንዲሰሩ ጥሪ ቀረበ

**ፍቃዱ ደሬሳና ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያውያን በአዲሱ ዓመት ለሰላም፣ እርቅና ሃገራዊ አንድነት ቅድሚያ ሰጥተው እንዲሰሩ የሃይማኖት አባቶች ጥሪ አቀረቡ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን፣ የአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች፣ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስና የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የ2015 ዓ.ም አዲስ ዓመት አስመልክተው የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል።

በመግለጫቸውም ግጭት ለማንም የማይበጅ አጥፊ በመሆኑ በአዲሱ ዓመት ኢትዮጵያውያን ለሰላም፣ እርቅና ሀገራዊ አንድነት ቅድሚያ ሰጥተው እንዲሰሩ ጠይቀዋል።

አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት አዲሱን ዓመት አስመልክተው በሰጡት መግለጫ፣ በአዲሱ ዓመት ከገባንበት አላስፈላጊ ግጭት ወጥተን ዘላቂ መፍትሔ ማምጣት ወደሚያስችል ምክክርና ውይይት መግባት ይኖርብናል ብለዋል።

በግጭት ችግሮቻችንን መፍታት አንችልም እንዲሁም በመራራቅም ማደግ አንችልም ያሉት ቅዱስነታቸው፤ በአዲሱ ዓመት ዘላቂ መፍትሔ ማምጣት ወደሚያስችል ምክክርና ውይይት መግባት ይኖርብናል ሲሉ ተናግረዋል።

አሮጌውን አስተሳሰብ እንዳለ ተሸክመን ለመቀጠል እየዳዳን ከሆነ አዲስ ዓመት ማለቱ የአፍና የጀሮ ቀለብ ከመሆን በቀር የሚሰጠን አንዳች ትርጉም የለም ያሉት ቅዱስነታቸው፤ በአዲሱ ዓመት አዲስ የሆነ የሰላም የዕርቅና የአንድነት እንዲሁም የፍትሕና የእኩልነት መርሕ አንግበን ፍጹም ሰላምን ለማንገሥ ማሰብና መነሣሣት አለብን ሲሉ ገልፀዋል።

የአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሼህ ሱልጣን አማን ኤባ በበኩላቸው፣ አዲሱን ዓመት በማስመልከት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት 2014 ዓመትን ጨርሰን ዛሬ የ2015 ዓ.ምን አንድ ብለን ጀምረናል። የተጠናቀቀውን ዓመት በተቆላለፈ ፈተና ውስጥ ሁነን ነው ያሳለፍነው። ካለፈው ዓመት ፈተና ፈጣሪ ረድቶን ህዝቡም በአንድነት በመቆም ይህን አልፈን እነሆ ወደ አዲስ ዓመት ተሸጋግረናል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በአዲሱ ዓመት የእርስ በእርስ ግንኙነታችንና አንድነታችን ይበልጥ አጠናክረን እንድንቀጥል መልዕክቴን አስተላልፋለሁ። ከውስጥም ሆነ ከውጭ ሰላማችንን የሚያደፈርሱ ኃይሎችን እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ ህዝቡ ከመንግሥት ጋር እጅና ጓንት

ኢትዮጵያውያን ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል

# «አዲሱን ዘመን ስንቀበለው እንደ መስከረም አደይ ተስፋችን እንደሚፈካ በመተማመን ነው»

- ዐቢይ አህመድ(ዶ/ር)

**ጌትነት ምህረቴ**

አዲስ አበባ፡- አዲሱን ዘመን በጉጉት ስንቀበለው እንደ መስከረም አደይ ተስፋችን እንደሚፈካ፣ እንደ አዝመራው ውጥናችን ፍሬ አፍርቶ እንደምናይ፣ እንደ በጋ ወንዝ ሰላማችን ከአደፍራሾች እንደሚጠራ፣ ጭጋግ ጭለማው ከላያችን ተገፍፎ ብርሃን እንደሚፈነጥቅብን በመተማመን ነው ሲሉ የኢፌድሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ አዲሱን ዓመት አስመልክተው ባስተላለፉት መልዕክት እንዳሉት ፤አዲሱን ዘመን በጉጉት ስንቀበለው እንደ መስከረም አደይ ተስፋችን እንደሚፈካ በመተማመን ነው። ይህ እምነታችን እንዲሳካ ከዘመኑ ጋር እኛም አብረን መቀየር ይኖርብናል። ምክንያቱም የእኛ መለወጥ ነው የዘመኑን ለውጥ እውነተኛ የሚያደርገው።

ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ፣ አሮጌ ምዕራፍ ተዘግቶ አዲስ ምዕራፍ ሲገለጥ፣ መጪውን ዘመን ልንቀበለው በምንዘጋጅበት በዛሬው የዋዜማ ምሽት ላይ ሆነን፣ ዐይነ ሕሊናችን ያሳለፍነውን ዓመት በትውስታ፣ መጪውን ደሞ በአዲስ ተስፋ ማስተናገዱ አይቀርም።

ያገባደድነውን ዓመት ስናስብ ትውስታችን በብዙ መልካምና እኩይ አጋጣሚዎች ተሞልቶ እናገኘዋለን። በአንድ በኩል ዓመቱ ጠላቶቻችን ግንባር ፈጥረው ጥቃታቸውን ያጠነከሩብን፣ ገሚሶቹ በሀገር ውስጥ ንጹሐን ለሞት ጭዳ ሲያደርጉ ጦር ያዘመቱበት፣ ገሚሶቹ በውጪ ዓለም አቀፍ ጫና በሚያሳድሩ መድረኮችና ሚዲያዎች አማካኝነት የቅጥፈት ዘመቻ ያጧጧፉበት፣ እንደ ሀገር የተፈተንበት ዓመት ነው።

በሌላ በኩል ተስፋችንን የሚያለመልሙ፣

«አዲሱን ዘመን ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል







# «አንድነት ኢትዮጵያ የቆመችበት አለት ነው»

- አቶ ደመቀ መኮንን
የኢፌዲሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- አንድነት ኢትዮጵያ የቆመችበት አለት ነው ሲሉ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ገለጹ። የመከላከያ ሚኒስቴር የአንድነት ቀንን አስመልክቶ " ስናስብር ስናምር " በሚል መሪ ቃል ትላንት ልዩ መርሐግብር አካሂዷል።

በመርሀ ግብሩ የተገኙት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን፤ አንድነት ለኢትዮጵያውያን ምን እንደሆነ ዓለም በጥልቅ የሚረዳው የአኩሪ ብሄራዊ ድሎች መሠረት እንዲሁም ኢትዮጵያ የቆመችበት አለት ነው ሲሉ ገልጸዋል። በዓሉ አንድነት የሚዘከርበትና በአዲሱ ዓመትም አንድነት ተጠናክሮ የሚቀጥልበት እንዲሁም ቃል የሚገባበት ነው ብለዋል።

ህብረት ጥንካሬና ውበት ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ እንደ ኢትዮጵያ ብዝኃነት ያለው አገር በልዩነት ውስጥ ያለውን አንድነቱን ሲያጠበቅ ውበቱ ጥልቅና የጎላ እንደሚሆን ተናግረዋል። አንድነት ለኢትዮጵያውያን ምን እንደሆነ ዓለም በጥልቅ የሚረዳው የአኩሪ ብሄራዊ ድሎች መሠረትና ኢትዮጵያ የቆመችበት አለት እንደሆነ አስታውቀዋል።

ሚኒስትሩ እንዳሉት፤ የኢትዮጵያውያን ልዩ ትሩፋት የሆኑት የጳጉሜን ቀናት አገርን በሚገነቡና ህብረ

«አንድነት ኢትዮጵያ ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል






«በኢትዮጵያውያን አንድነትና ቁርጠኝነት የጠላቶቻችን እኩይ ዓላማ ሳይሳካ ቀርቷል»

- አቶ አደም ፋራህ
የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት

ገጽ 5

# አዲሱ ዓመት ለሀገራችን ከፍታ የምንተጋበት ሊሆን ይገባል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ ፡- አዲሱ ዓመት ለሀገራችን ከፍታ የምንተጋበት፣ የተቸገሩ ወገኖቻችንን የምንረዳበት የመተሳሰብ እና የአንድነት ዓመት እንዲሆን የክልል ርዕሰ መስተዳድሮች መልካም ምኞታቸውን ገለጹ። የ2015 ዓ.ም አዲስ ዓመት በማስመልከትም የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል።

የደቡብ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ርስቱ ይርዳው የ2015 ዓ.ም አዲስ ዓመት በማስመልከት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል። በመልዕክታቸውም፣ አዲሱ ዓመት ለሀገራችን ከፍታ የምንተጋበት፣ የተቸገሩ ወገኖቻችንን የምንረዳበት የመተሳሰብ እና የአንድነት ዓመት እንዲሆን መልካም ምኞታቸውን ገልጸዋል።

አዲሱ ዓመት ለኢትዮጵያ የከፍታ ዘመን፣ ለሕዝቦቿ አንድነት እና ዘላቂ ሰላም የሚሰፍንበት ዘመን እንዲሆንም ተመኝተዋል። በአዲሱ ዓመትም የሕዝብ አንድነት፣ መተሳሰብ እና ድጋፍ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ርዕሰ መስተዳድሩ ጥሪ ማቅረባቸውን ከክልሉ መንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽህፈት ቤት ያገኘው መረጃ ያመለክታል።

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ አሻድሊ ሀሰን፣ አዲሱ የ2015 ዓ.ም ከምንም በላይ የዜጎችን ሰላም እና ደህንነት ለማስጠበቅ እና የልማት እና የመልካም አስተዳደር ሥራዎችን ውጤታማ ለማድረግ የሚሠራበት ዓመት ሊሆን እንደሚገባ ገልጸዋል።

ርዕሰ መስተዳድሩ አዲሱን ዓመት በማስመልከት በሰጡት የመልካም ምኞት መግለጫ፣ የ2015 ዓ.ም ፍቅር፣ አንድነት እና መተሳሰብ የተሞላበት ዘመን እንዲሆን ተመኝተዋል።

አዲሱ ዓመትም የላቀ ማኅበራዊ አንድነት፣ ወንድማማችነት እና ዘላቂ ሰላም እንዲኖር ተግተን የምንሠራበት ዓመት ሊሆን ይገባል ሲሉ ርዕሰ መስተዳድሩ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።አሸባሪው ሕወሓት ለ3ኛ ጊዜ የከፈተውን ጦርነት በመመከት በመጭው ዓመት ልማታችን ላይ እንድናተኩር ሕዝቡ የጀመረውን አኩሪ የደጀንነት ተግባር አጠናክሮ እንዲቀጥል የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ይልቃል ከፋለ ጠይቀዋል።

አሸባሪው ሕወሓት ዳግም ስጋት እንዳይሆን አድርጎ በመመከት በመጪው ዓመት ልማት ላይ እንድናተኩር ህዝቡ የጀመረውን አኩሪ የደጀንነት ሚናም አጠናክሮ እንዲቀጥል ዶክተር ይልቃል ጥሪ አቅርበዋል።

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ የ2015 ዓ.ም አዲስ ዓመትን አስመልክተው የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላለፉ።

በአዲሱ ዓመት ከምንም በላይ ከመልካም ተሞክሮዎቻችንና ከፈተናዎቻችን ትልቅ ትምህርት በመውሰድ፣ ተስፋን በመሰነቅ ለአዲስ ሕይወት ራሳችንን የምናዘጋጅበት ይሆናል። ተለዋዋጭ በሆነ የጊዜ ዑደት ውስጥ የሚያጋጥሙን ፈተናዎችና መልካም ዕድሎች ሁሉ በማለፍ አዲስ የሕይወት ተስፋን የሚያሰንቅ አዲስ ዓመት መድረስ መታደል ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ለመላው የኦሮሞ ሕዝብ፣ በአገር ውስጥና በውጭ ላላችሁ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ዕድለኞች ናችሁና እንኳን ለ2015 ዓ.ም አዲስ ዓመት በሠላም አደረሳችሁ ለማለት እወዳለሁ ብለዋል።

በአዲሱ ዓመት ሠርተን ውጤት የምናስመዘግብበት፣ ነግደን የምናተርፍበት፣ ሁለንተናዊ ብልፅግናን እውን ለማድረግ ጠንካራ መሠረት የምንጥልበት፣ ከሁሉም በላይ ህብረብሔራዊ ወንድማማችነት በተጠናከረ ሁኔታ ሰርፆ ዘላቂ ሠላም የሚሰፍንበት ዓመት እንዲሆንልን እየተመኘሁ በድጋሚ እንኳን ለ2015 አዲሱ ዓመት በሠላም አደረሳችሁ ለማለት እወዳለሁ ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር አቶ አወል አርባ ለአዲስ ዓመት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል።

የርዕሰ መስተዳድሩ አዲሱ 2015 ዓመት የጀመርናቸው የልማት፣ የዴሞክራሲና የብልፅግና ጉዟችንን አጠናክረን ኢትዮጵያችንን ወደ ተሻለ ከፍታ የምናሸጋግርበት፣ ከጦርነት ከጥላቻ ይልቅ ለሰላም እና ለፍቅር የምንሰራበት፣ ድህነት እና ኋላ ቀርነትን በማስቀረት ወደ እድገት መስመር የምንገባበት፣ ህብረ ብሄራዊ አንድነታችንን በማጠናከር ልዩነቶቻችንን ባከበረ መልኩ የሀገራችንን ሉአላዊነት አስከብረን ወደ ቀጣዩ ዓመት የምንሸጋገርበት እንዲሆን ከምኞት ባለፈ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የራሱን ጡብ የሚያስቀምጥበት ግንባታ ሊሆን ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

የሶማሌ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሙስጠፌ መሀመድ አዲሱን ዓመት ምክንያት በማድረግ የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል። ርዕሰ መስተዳድሩ በመልዕክታቸው፣እንደ ሀገር ባለፉት አራት ዓመታት በርካታ እንቅፋቶችና መሰናክሎች ያጋጠሙ መሆኑን አስታውሰዋል። ይሁን እንጂ በጋራ እና በአንድነት በመቆም አገር እንድትበተን የተሸረቡ ሴራዎችን በማክሸፍ አሁን ያለንበት ደረጃ ላይ እንገኛለን ነው ያሉት አቶ ሙስጠፌ።

በአዲሱ ዓመትም የገጠሙንን የውስጥና የውጭ ጠላቶቻችን እኩይ ሴራ በመሻገር ለኢትዮጵያ ሰላም የሚመጣበት፣ ለህዝቦቿም የመረጋጋት ዘመን እንዲሆን መመኘታቸውን ከክልሉ ኮሙኒኬሽን ያገኘነው መረጃ ያመላክታል።




# አየር ኃይሉ ለአገር ሉዓላዊነት አስተማማኝ ዘብ ሆኗል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ አየር ኃይል ለአገር ሉዓላዊነት አስተማማኝ ዘብ የሚያደርገውን ትልቅ ራእይ ሰንቆ በመስራት ስኬታማ መሆኑን ዋና አዛዡ ሌተናል ጄነራል ይልማ መርዳሳ ገለጹ።

የኢትዮጵያ አየር ኃይል ዋና አዛዥ ሌተናል ጄነራል ይልማ መርዳሳ አየር ኃይሉ ትናንት የአንድነትን ቀን ሲያከብር እንዳሉት፤ በ2014 ዓ.ም አየር ኃይል በኢትዮጵያ ህልውና ላይ ተደቅኖ የነበረውን አደጋ በመመከት ረገድ ደማቅ ታሪክ ጽፏል። በአየር ኃይሉ ላይ የተከናወነው የለውጥ (ሪፎርም) ሥራዎች ውጤታማ ናቸው፤ በዚህም አየር ኃይሉ ለአገር ሉዓላዊነት አስተማማኝ ዘብ እየሆነ ነው።

የኢትዮጵያን ህልውናና ሉዓላዊነት በማስጠበቅ ረገድ የአየር ኃይል አባላት ከፍተኛ ጀብዱ መፈጸማቸውንም አብራርተዋል። የኢትዮጵያን አየር ክልል በመጣስ ለአሸባሪው ሕወሓት መሳሪያ ለማቀበል የሞከረ የጦር አውሮፕላን ላይ የተወሰደውን እርምጃም ለአብነት አንስተዋል።

"የኢትዮጵያ አየር ኃይል የጥንካሬ ምንጭ አንድነት ነው" ያሉት ሌተናል ጄነራል ይልማ መርዳሳ፤ በቀጣይም አንድነታችንን በማጠናከር የአየር ክልላችንን በአስተማማኝ ሁኔታ ለመጠበቅ ከመቼውም ጊዜ በላይ ዝግጁ ነን ብለዋል።

"የኢትዮጵያ አየር ኃይል የጥንካሬ ምንጭ አንድነት ነው፤ አንድነታችንን ይበልጥ በማጠናከር የትኛውንም አይነት ጥቃት በብቃት ለመመከት ዝግጁ ነን" ሲል የኢትዮጵያ አየር ኃይል የአንድነት ቀንን በተለያዩ መርሐግብሮች ማክበሩን የዘገበው ኢዜአ ነው።

በመርሐግብሩ የኢትዮጵያ አየር ኃይል ዋና አዛዥ ሌተናል ጄነራል ይልማ መርዳሳ፣ የቢሾፍቱ ከተማ ከንቲባና ሌሎች እንግዶች የታደሙ ሲሆን ከፍተኛ መኮንኖች ማዕረግ የማልበስ፣ የአየር ኃይል ሠራተኛ ቤተሰቦች ድጋፍ ማድረግና የእውቅና መርሐግብር ተከናውኗል።



አቶ ሙስጠፋ ትኩ



አቶ ሙሉነህ ፈይሳ

# የአንድነት ቀን ህብረብሄራዊ አንድነትን ባከበረ መልኩ ተከበረ

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- የአንድነት ቀን ህብረብሄራዊ አንድነትን ባከበረ በአዲስ አበባ በተለያየ ክፍለከተሞች ተከብሯል።

በንፋስ ስልክ ላፍቶ በተካሄደው የአንድነት ቀን በዓል ላይ የክፍለ ከተማው የፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ አቶ ሙስጠፋ ትኩ እንደተናገሩት፣ አዲስ ዘመንን ስንቀበል ተደጋግፈን የበጎነት ቀንን በማሰብ፣ አምራችነታችንን አጠናክረን፣ ለሰላም ቆመን እና ተሰልፈን፣ በአገልጋይነት መንፈስ ተደምረን ኢትዮጵያዊ አንድነታችንን በብዝሃነታችን አድምቀን ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ ለዘመናት ፈተናዎችን እያለፈች ለኃያላን አገራት ሳትንበረከክ የነጻነትና የድል ተምሳሌት በመሆን ከራሷ አልፋ ለአህጉራዊ አንድነት የታገለች እና አንድነቷን አጠናክራ የቀጠለች አገር መሆኗን የገለጹት አቶ ሙስጠፋ፣ በበርካታ የተፈጥሮ ሀብት እና በህዝብ ብዛት የታደለች መሆኗን አስታውሰዋል።

ታሪካዊ ጠላቶቿ የህዝብ አንድነቷ እና የተፈጥሮ ሀብቷን፣ እንዳትጠቀም በቀጥታ ወረራ አልሳካ ሲላቸው በውስጥ ተላላኪ እና ባንዳዎች በተናበበ መልኩ ጥቃት ቢደቅኑም መንግሥት እና ህዝብ በንቃት በመከታተል አንድነት እና የሀገር ፍቅርን በመላበስ እያሸነፍን መሆኑን ጠቁመዋል።

ለዓላማችን ስኬት ተጨባጭ ውጤት በማሳየት ለሚመጡ ፈተናዎች ተደምረን በአንድነት አገራችንን፣ ከተማችንን ወደ አዲስ ከፍታ ለማስቀመጥ የምንተጋበት ዓመት መሆኑንም አመላክተዋል።

የኢትዮጵያዊ አንድነት መገለጫ የሆነው የአዲስ አበባ ከተማ በ2013 በጀት ዓመት የአዲስ ተስፋ ችቦ ይዞ በ2014 ብዙ ድሎችን ተጎናጽፏል ሲሉም አስታውሰዋል። በ2015 በጀት ዓመት አንድነታችንን በመደመር አጠናክረን የያዝነውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ተግተን እየሰራን ነው ብለዋል።

የንፋስ ስልክ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ሙሉነህ ፈይሳ በበኩላቸው፣ ኢትዮጵያ ከሌላው ዓለም በተለየው ዘመን አቆጣጠሯ ባላት 13ኛ የጳጉሜን ወር በክፍለ ከተማው የተሰሩ በጎና መልካም ሥራዎችን ጠቁመዋል።

በአምስት ቀናቱ 39 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የተደረገበት የተለያየ የበዓል መዋያ ስጦታዎች፣ ለ385 አባወራዎች የቤት እድሳት፣ አንድ ቤተ-መፃህፍትን ጨምሮ የ70 አባወራዎች የአዲስ ቤት ግንባታ 129 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የተደረገባቸው ሥራዎች መሰራታቸውን ገልጸዋል። በዚህ ተግባር የተሰማሩ በጎ ፈቃደኞችን በሙሉም አመስግነዋል።

አንድ ስንሆን የሚፈጠረውን የሚያውቀው ጠላት የሚከፋፍለንን አጀንዳ በማቀበል እና በተለያየ የሀሰት ፕሮፓጋንዳ አንድነታችን እንዲላላ፣ በጥርጣሬ እንድንተያይ ሌት ተቀን እየሰራ መሆኑን ገልጸዋል። በመሆኑም አንድነታችን እና ህብረታችን ለጠላት ሽንፈት መለያየታችን ደግሞ ለጠላት ድል መሆኑን በማወቅ አንድነታችንን ማጠናከር አለብን ሲሉም ተናግረዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## አዲስ ዘመን፣ አዲስ ዓመት፣ አዲስ ተስፋ!

የኢትዮጵያውያን ነጻነትና አይበገሬነት የአገርን ሉዓላዊነት አስከብሮ ከመኖር፣ እንዲሁም ከኪነ ሕንጻና ኪነጥበብ ትውፊት ባለቤትነታቸው ባሻገር፤ በዓለም ላይ የራሳቸው የዘመን ቀመር ቀምረው ዘመንን ከሚለውጡ ጥቂት ሕዝቦች መካከል ናቸው። ይህ ብቻ አይደለም በስነ ፈለግ እውቀታቸው ቀድመው በራሳቸው የእውቀት ልኬት "የ13 ወር" ባለቤት ተብለው የሚጠሩ ብቸኛ ሕዝቦችም ናቸው። ታዲያ በዚህ መልኩ ታላቅና ቀደምት ሕዝቦች ሆነው የሚገለጹት ኢትዮጵያውያን፤ የነጻነት ቀንዲልነት፤ የኪነጥበብ ባለቤትነት፤ የእኔ የሚሉት የሥነ ጽሑፍና የዘመን ቀመር ፈጣሪነታቸው እውነት ቢሆንም በተለያየ መልኩ መፈተንና በችግር ውስጥ መራመድም ግድ ሆኖ ዘመናትን አሳልፈዋል።

የፈተናቸው ምክንያት፣ የችግራቸው መሰረት ውሉ እዚህ ጋ ነው ባይባልም፤ አንድም በውስጥ በሚነሱ ችግሮች፤ ሌላም ከውጭ በሚደረጉ ኢትዮጵያን የማዳከም ሴራዎች፤ የባንዳና ታሪካዊ ጠላቶች የሴራ ጥምረት ቀዳሚውን ሚና ይጫወታል። በዚህ ረገድ ባለፉት ዓመታት በእጅጉ ስትፈተን የቆየችው ኢትዮጵያ፤ አሁን ደግሞ የአሸባሪነት ሰብዕናን ተላብሰው ባንዳዎች የከፈቱባትን ጦርነት በመመከት ላይ ትገኛለች። ልጆቿም ምንም እንኳን ሰላምን አብዝተው ቢሹምና ልማትን አብዝተው ቢመኙም፣ በአንድነት ከፍ ማለትን አብዝተው ቢፈልጉም፤ የተከፈተባቸው ጦርነት ይሄን የሚቀለብስ ስለሆነባቸው የሃገራቸውን አንድነት ለማስጠበቅ በጦር አውድ እየተዋደቁ ይገኛሉ።

እንዲህ እንደ ዛሬው አዲስ ዓመት ሲሆን ደግሞ የሰው ልጅ ሁሌም አዲስ ነገርን ማለሙ፣ አዲስ ተስፋ መሰነቁ፣ አዲስ ሕልምና ምኞት ይዞ ለተሻለ ነገ መራመዱ ተፈጥሯዊ ባህሪው ነው። ለዚህ ደግሞ በፈተና ውስጥ መልካም እድልን፤ በመከራ ውስጥ አሻጋሪ መፍትሄን፤ በጨለማ ውስጥ ከፊት ለፊት ብልጭ እያለች ያለች ብርሃንን ማየትአብዝቶ ይፈልጋል። ኢትዮጵያውያንም ዛሬን እየተመኙም፣ እየፈለጉም፣ እያደረጉም ያሉት ይሄንኑ ነው። ምክንያቱም፣ ኢትዮጵያ ከፈተናዎቿ ልቃ እንድትታይ፣ ኢትዮጵያውያንም ከፈተናዎቻቸው ከፍ ብለው በአሸናፊነት እንዲሻገሩ ከመሻት በዘለለ፤ ሲፈተኑ በፈተና ውስጥ ጸንተው የፈተና መሻገሪያ ስልትና ኅብረትን እየፈጠሩ፣ በመከራ ውስጥ የመከራውን ግዝፈት ሳይሆን ያሉትን ዕድሎች እየፈለጉ የመከራውን ማለፊያ ድልድይ ሰርተው ፈተናውን በዕድል፣ መከራውንም እንደ ምክር ተጠቅመው ዛሬ ደርሰዋል።

በዚህ ረገድ የተጠናቀቀው 2014 ዓ.ም በብዙ ፈተናዎች፣ በብዙም መከራዎች ውስጥ እየተሻገሩ፤ እንደ ሕወሓት፣ ሸኔና አልሸባብ ያሉ የሽብር ቡድኖች ተቀናጅተው የፈጠሩባቸውን ዘርፈ ብዙ ጦርነት እየመከቱና እያከሸፉ በድል እየተራመዱ፤ በጦርነት ውስጥ ስለ ሰላምና አብሮነት ደጋግመው እየተማጸኑ፤ ስለ ኢትዮጵያ ከፍታ፣ ስለ ኢትዮጵያውያን አብሮነት ዋጋ እየከፈሉ አሳልፈዋል። ጠላቶቻቸው በጦርነት ወጥረው ከልማታቸው ሊጎትቷቸው፤ ከብልጽግና ግስጋሴያቸው ሊገቷቸው፤ የሰላም አየር ነፍገው፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ፈጥረው ሊያናውጧቸው በብዙ ጣሩ። ኢትዮጵያውያን ግን በአንድ እጅ የልማት ሥራቸውን እያከናወኑ፤ በሌላ እጅ የጠላትን ጥቃት እየመከቱ በፈተና ውስጥ ድልን፤ በመከራ ውስጥ ስኬትን እያስመዘገቡ ቀጥለዋል።

ዛሬም አዲሱን ዓመት አንድ ብለው ሲጀምሩም፤ ከትናንት ፈተናዎች የተፋታ፣ ከመከራ የተለያየ፣ ከፀብና ጦርነት የተቆራረጠ፣ ከስደትና ሞት የተራራቀ፣ በጥቅሉ የመከራው ዘመን አልፎ የብሩህ ተስፋ ዘመን እንዲሆንላቸው ከፍ ባለ መመኘት ውስጥ ሆነው ነው። "የጎመን ምንቸት ውጣ፣ የገንፎ ምንቸት ግባ" ብለው ዘመናቸውን በብርሃን ችቦ ሲዋጁም፣ ይሄው የመከራና ችግር ዘመን እንዲያበቃ፤ እና የሰላም፣ የፍቅር፣ የአብሮነትና የብልጽግና ዘመን እንዲተካላቸው በእጅጉ በመሻት ነው። ተገድደው የገቡበት ጦርነት እንዲያበቃ፤ የክፉዎች ሴራና ተንኮል ፈርሶ ሕዝብ በአንድ እንዲሰባሰብ፤ የተጀመረው የልማት መስመር ሳይቆራረጥ እንዲቀጥል፤ የከበደው የዜጎች ኑሮ እንዲቀልል፤ የተዛባው ትርክትና አመለካከት በፍቅርና አንድነትን በሚሰብኩ ትርክቶች እንዲቀየር፤... አብዝተው ለመስራት ራሳቸውን የሚያዘጋጁበትም ነው።

ይህ እንዲሆን ደግሞ ኢትዮጵያውያን የ2015 ዓ.ም የመጀመሪያው ገጽ ላይ ቆመው መከተብ የጀመሩትን መልካም ሕልምና ብሩህ ተስፋ የበለጠ አድምቀው በማስቀጠል ውብ ታሪክን የሚያስከትቧቸው 364 ንጹህ ገጾች ከፊት ይጠብቋቸዋል። እነዚህ ንጹህ ገጾች በንጹህ ልብ፣ በቅን አስተሳሰብና ተግባር የታገዘ መልካም ነገር እንዲጻፍባቸው የማድረጉም፤ ከዚህ በተቃራኒው የሆኑ ክፉ የታሪክ ትውስታዎችን ፍቆ ፍቅርን መላበስም የቀናቱ ባለቤት ሕዝቦች ድርሻ ነው። ምክንያቱም ጥያቄው እነዚህን ንጹህ ገጾች ካለፈው ዓመት የተሻለ እና ለቀጣዩ ጉዞ ጠንካራ መሰረት የሚጥሉ ምን መልካም ነገሮች እንዲጻፍባቸው ይደረግ? የሚለውን መመለስ ነውና። የአዲሱ ዘመን አዲስ ተስፋም እዚሁ ላይ የሚመሰረት ነው።

እናም አዲስ ዓመት በመቀበል ውስጥ የተለወጠ ማንነት፣ ከክፋትና ጥፋት የተላቀቀ ሰብዕና፣ ስለ ሰው ልጆች ከፍታ እንጂ ውድቀት የማያሰብ አዕምሮ፣ ቅድሚያ ለሃገር ማሰብንን መስዋዕት መሆንንና በአጠቃላይ በሁሉም መስክ የአሸናፊነት ስነልቦናን የምንጎናጸፍበት ሊሆን ይገባል። በአዲስ ዘመን አዲስ ተስፋን ስንይዝም፤ በፈተናዎች ያለመውደቅ፤ ለመከራዎች ያለመንበርከክ፤ ለክፋት በትሮች የሰላም እጅን ከፍ አድርጎ በማሳየት ክፋትን የማሸነፍ፤ ባለፉ ክፋቶችና ስህተቶች ተሸብቦ ለሌላ ጥፋትና መከራ ራስንም ወገንንም ያለማጨት ልዕልናን፤... አጥብቆ በመግዛት ሊሆን የተገባ ነው። ይህ ሲሆን ነው የጎመን ምንቸት ወጥቶ፣ የገንፎ ምንቸት የሚገባው ዘመኑ የእውነት አዲስ እና ተስፋን የተሞላ የሚሆነው!


## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

# አዲስ አመት የሰላም ፤ የጀመርነውን የብልጽግና ጉዞ አጠናክረን የምናስቀጥልበት እንዲሆንልን...

**ስምስም ምንግሥቱ**

ደመናው በጭጋግ ተሸፍኖ፣ የእርሻ ማሳው በሰብል ተሸፍኖ፣ ምድር አረንጓዴ ለብሳ የአይን መስህብ የምትሆንበት፤ ሰዎች የተዘራ ዘር ለፍሬ በቅቶ የጥጋብ ዘመን እንዲሆን የሚመኙበት የክረምት ወቅት መውጣት በብዙዎች ዘንድ ይናፈቃል። ዛሬ ዘመን ሰልጥኖ መሻገሪያ ድልድይ ተሰርቶና መጓጓዣውም ተመቻችቶ እንጂ በክረምቱ በሚሞላ ወንዝ ምክንያት መሻገሪያ ጠፍቶ ዘመድና ወዳጅ ለወራት መለያየት ግድ እንደነበርና ክረምቱ ሲወጣ በናፍቆት እንደሚገናኙ ታሪክ ያስታውሰናል።

ደመናው ገልጦ ብርሃን ሲሆን፣ ወቅት ሄዶ ወቅት መተካቱ ብቻ ሳይሆን፣ የሰዎች ተስፋም አብሮ ይለመልማል። ባለፈው ያጡትን ለማግኘት፣ ለሕይወት መስመራቸው የሚሆነውንም ለማቀድ፣ የተበላሸ ሕይወት ከነበራቸውም ለማስተካከል ቃል የሚገቡት ዘመን ሲለወጥ ነው። እንዲህ ያለው ተስፋና ቸር ምኞት በኢትዮጵያውያን የተለመደ ነው።

በመገናኛ ብዙሃን ሳይቀር ሰዎች የአዲስ ዓመት እቅዳቸውን፣ ተስፋቸውንና ምኞታቸውን እየተጠየቁ ለሌሎች ትምህርት ሆኖ ማስተላለፉም እንደ አንድ ባህል ተወስዷል። ይህ ሁሉ ተስፋና ምኞት የሚሰምረው ግን ሀገር ሰላም ስትሆን እንደሆነ አሁን ኢትዮጵያ ሀገራችን ካለችበት ነባራዊ ሁኔታ መገንዘብ ይቻላል።

ሰዎች እየተጨነቁና እያሰቡ ያሉት በአዲሱ የዘመን መለወጫ ስላቀዱት ሰለነገ የሕይወት መስመራቸው ወይንም አዲሱን ዓመት በምን ሁኔታ እንደሚቀበሉት ሳይሆን፣ ዛሬን ውለው ስለማደራቸውና በሕይወት ስለመቆየታቸው ነው። በዚህ ወቅት አርግጠኛ ከሚሆነው ሰው ይልቅ ‹‹እስኪ ቆይ›› የሚለው ሰው በዝቷል።

በተለይም የጦርነት ወላፈኑ በደጃቸው እያለፈ ከነገ ዛሬ ምን እሆን ይሆን? እያሉ ለሚጨነቁ በቅርብ ቤተሰባቸውና ወገናቸው ላይ ሞትና ስቃይ ምን እንደሆነና የመደፈር ወንጀልን እያዩ ለሚያሳልፉ፣ የጉዳቱ ሰለባ ጭምር ለሚሆኑ ከመናገርም በላይ ነው ችግሩ። ‹‹ጆሮ ሲመታ አይን ያለቅሳል›› እንዲሉ አንጻራዊ ሰላም ባለበት የሀገሪቱ ክፍል የሚኖረው ዜጋም ቢሆን በሥነልቦና እየተጎዳ ነው።

የጦርነት ወላፈኑ ባይደርስብትም ወገኑ በሞትና በስቃይ ውስጥ ሆኖ እንቅልፍ ሊተኛ አይችልም። የጦርነት ወላፈኑ እንደማይደርስበትም እርግጠኛ መሆን አይቻልም። ኢትዮጵያውያን እንዲህ ያለው ስጋት ውስጥ እንዲወድቁ ያደረጋቸው ጉዳይም ግልጽ ነው።

ሰዎች በመኖርና ባለመኖር መካከል ሆነው የእለት ኑሮአቸውን በሰቆቃ እንዲያሳልፉ፣ ቀያቸውን ለቀው እንዲሰደዱ፣ ኀዘንና ምሬት እንዲያደቃቸው፣ የመሳሪያ ድምጽ በመስማት ሞታቸውን እንዲያስቡ፣ በወገናቸው ስቃይ ቅስማቸው እንዲሰበር፣ ብቻ የሰው ልጅ በቃላት መግለጽ በማይቻል ሁኔታ ውስጥ እንዲሆን ያደረገው በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ጦርነት የከፈተው አሸባሪው ሕዝባዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይ (ትህነግ) ነው።

ቡድኑ አምና ከፊሉ በሬውን ጠምዶ ለእርሻ ሥራ ዝግጅት እያደረገ፣ ከፊሉም የእርሻ ሥራውን ጀምሮ በነበረበት ወቅት የጦርነት ነጋሪት ጎስሞ ህዝብን ለእልቂት፣ የግለሰብ፣ የመንግሥትና የሕዝብ ንብረት ለውድመት ዳርጓል። ተምረው ሀገራቸውን ይጠቅማሉ የተባሉ ሕጻናትና ታዳጊዎችን ለጦርነት ማግዷል።

በጦርነቱ የህክምና መስጫዎችን፤ ለዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠርና ለሀገር የኢኮኖሚ እድገት ገቢ በማስገኘት አስተዋጽኦ የነበራቸውን ፋብሪካዎች በማውደም በሀገርና በሕዝብ ላይ ተዘርዝሮ የማያልቅ ጥፋት ፈጽሟል።

በዜጎችም ላይ በተለይም ከኢትዮጵያውያን የማይጠበቅ በአይን ለማየት፣ በጆሮ ለመስማት የሚቀፍና ዘግናኝ የጭካኔ ድርጊቶችን ፈጽሟል፤ ለሕዝብ ቆሜያለሁ የሚል የሀሰት ፕሮፓጋንዳ እየነዛ፣ አስተዳድርሃለው፣ እታገልልሃለው ለሚለው ሕዝብ እንኳን ሳይራራ የትግራይን ሕዝብ የከፋ መከራና ስቃይ ውስጥ ከቷል።

ይህንኑ እኩይ የጥፋት ድርጊቱን የመንግሥትን የሰላም እጆች በመርገጥ ለሶስተኛ ጊዜ በሀገር ላይ ጦርነት በማወጅ ቀጥሎበታል። አብዛኛው የግብርና ሥራ ተጠናቅቆ ዳር ለመድረስ የቀናት እድሜ በሚጠበቅበት፣ ዜጎችም መንግሥት የጀመረው የሰላም መንገድ ሰምሮ ከጦርነት እሳት ውስጥ የሚወጡበትን እየናፈቁ ባለበት ወቅት ለሰላም የተዘረጋውን እጅ ረግጦ የተለመደውን የሰው ፍጅትና ሀብት ንብረት ማውደሙን ተያይዞታል።

ቡድኑ ትግራይ ሕዝብ የሚላከውን ሰብአዊ ድጋፎች በመዝረፍ ለጦርነት እያዋለ ይገኛል። በቅርቡን በአደባባይ ለሰብአዊ ድጋፍ ሊውል የተከማቸ ነዳጅ በመስረቅ በዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ አሰፋሪ የተባለውን የወንጀል ድርጊቱ በአደባባይ ፈጽሟል። ይህንንም አይኑን በጨው አጥቦ ለማስተባበል ሞክሯል። ‹‹የሌባ አይነደረቅ መልሶ ልብ ያድርቅ›› እንደሚባለው።

ጥፋቱ ተነግሮ የማያልቀው ይህ ቡድን እንኳንስ የበዓል አዲስ ተስፋን ይቅርና የነገ የሰው ልጅ ህልውናንም ለማጨለም የተነሳ በመሆኑ ዜጎች ቡድኑን የጀመረው ጦርነት በድል ፍጻሜ እንዲያገኝ በሚችሉት ሁሉ ሊንቀሳቀሱ ይገባል። ስለ ነገ ተስፋቸው ቡድኑን አምረው ሊታገሉት ያስፈልጋል።

‹‹ወርቅ በእሳት ይፈተናል›› እንደሚባለው ሕዝባችን ስለ ሀገሩና ስለቀጣይ ተስፋዎቹ በአንድነት በመቆም የሚያጋጥሙትን ተግዳሮቶች በሙሉ በጽናት አሸንፎ የሚሻገርበትን አቅምና ቁርጠኝነት መፍጠር ይኖርበታል። ለዚህም የሚሆን ዝግጁነት በየእለቱ መፍጠር ይጠበቅበታል።

‹‹በጥባጭ ካለ ማንም ጥሩ ውሃ አይጠጣም›› ቢባልም ዘመን ከዘመን መሸጋገራችን አንድ ተስፋ ነውና ዘመኑን በደስታ መቀበሉ በራሱ ተስፋ ይሰጣል። የተስፋ ሌላው ተስፋ ማድረጊያውና ማከሚያ መንገዱ ዛሬ በጦርነቱ ቀያቸውን ለቀው በማይመች ሁኔታ በመጠለያ ውስጥ የሚገኙትን፣ በተለያየ ምክንያት ችግር ውስጥ የወደቁትን በሚቻለው ሁሉ በማገዝ ነው።

በዚህ የጦርነት ጊዜ ውስጥ ሆነን ቸር መመኘታችንን አናቆምም። ለሰው ልጅ የተሰጠው ትልቁ ተስፋ በመሆኑም በጦርነት ለስቃይ የተዳረገው ሕዝብና የደቀቀው ኢኮኖሚ መልሶ እንዲያገግም የጦርነቱ መቆም ትልቁና ዋነኛው ቢሆንም ሰዎች የእለት ተእለት ተግባራቸውን በማስቀጠልና የልማት ተሳትፎቸውንም በማጠናከር ኢትዮጵያን ማስቀጠል ይኖርባቸዋል።

በጦርነት ውስጥም ሆነን እንደሀገር ያሳካናቸው እና ዓለም አቀፍ እውቅና ያስገኘልን የልማት ስራዎች አሉ። እነዚህን ስኬቶች 2015 ዓ.ም አጠናክረን በማስቀጠል አዲሱ ዓመት የበለጠ የስኬት ዘመን እንዲሆን ልንተጋ ይገባል። አዲስ ዓመት የጀመርነውን የብልጽግና ጉዞ አጠናክረን የምናስቀጥልበት የልማት ጊዜ እንዲሆንልን ብርታቱንና ጉልበቱን እንድንታደል ምኞቴ ለሁላችሁም ይሁን።

**መልካም አዲስ ዓመት ።**




ለመላው የኢትዮጵያ ህዝቦች እንኳን ለ2015 አዲስ አመት በሰላም አደረሳችሁ፣ አዲሱ አመት የሰላም፣ የጤና፣ የፍቅር የመከባበርና የመተሳሰብ ዘመን እንዲሆን መልካም ምኞታችንን እየገለጽን፡፡
አዲሱ ዘመን ኢትዮጵያ የጀመረችውን የለውጥ ጉዞ በላቀ ደረጃ የምታሳካበትና ሰላሟን ለማረጋገጥ ዘብ የምትቆምበት፣ ችግሮቻችንን በውይይትና በምክክር በሰከነ መንፈስ የምንፈታበት ዘመን እንዲሆን እንመኛለን፡፡
የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ሀገራችን የሰነቀችውን ራዕይ እውን እንዲሆን አዳዲስ የጥናትና ምርምር ስራዎችን በማከናወን እንዲሁም በስራ ላይ ያሉ ፖሊሲዎችን ክፍተቶችንና ማነቆዎችን በመለየት ችግር ፈቺ እና ተቀባይነት ያላቸው የፖሊሲ ምክረ ሃሳቦችን ለማቅረብ ዝግጁ መሆናችንን እየገለጽን፡፡

ኢንስቲትዩታችን በአዲሱ አመት በላቀ ደረጃ ለመፈጸም የአሰራር የአደረጃጀት እንዲሁም የለውን ብቁ የሰው ሀብት በመጠቀም ዓላማችንን ለማሳካት በኢኮኖሚና በማህበራዊ የጥናትና ምርምር ዘርፍ በኩል ያለውን ክፍተት በመሙላት ከምን ጊዜውም በበለጠ ጉልህ አስተዋጽኦ ለማበርከት ዝግጁ መሆናችንን እየገለጽን፣ ከኢንስቲትዩታችን ጋር በትብብር አብራችሁ ለመስራት ለምትፈልጉ ሁሉ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡

መጪው አዲስ አመት ለሀገራችን ዕድገት ለህዝባችን ሰላም፣ የሚሆንበት፣ በሀገር ደረጃ ለገጠሙን ወቅታዊ ሀገራዊ ችግሮች በመተባበር አማራጭ መፍትሄዎችን በማስቀመጥ የምንቀርፍበት፣ ሀገራችን አሸናፊ ሆና እንድትገኝ የምንጥርበት መልካም ፍሬ የምንሰበስብበት አዲስ ዘመን እንዲሆንልን እንመኛለን።

**መልካም በዓል**

# የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲቲዩት

ዜና

# «በኢትዮጵያውያን አንድነትና ቁርጠኝነት የጠላቶቻችን እኩይ ዓላማ ሳይሳካ ቀርቷል»

- አቶ አደም ፋራህ
የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት

**ፋንታነሽ ክንዴ**



አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያውያን የአገርን ነጻነትና ክብር ለማስጠበቅ ባሳዩት አንድነትና ቁርጠኝነት የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶችና የውስጥ ባንዳዎች እኩይ ዓላማ ሳይሳካ መቅረቱን የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አደም ፋራህ ገለጹ።

አቶ አደም ፋራህ የ2015 ዓ.ም አዲስ ዓመትን አስመልክተው ባስተላለፉት የእንኳን አደረሳችሁ መልእክት እንዳሉት፤ በተጠናቀቀው 2014 ዓ.ም የውጭ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶችና የውስጥ ባንዳዎችና ተላላኪዎች በመተባበር ኢትዮጵያን ፈትነዋታል። ሆኖም ኢትዮጵያውያን የአገርን ነጻነትና ክብር ለማስጠበቅ ባሳዩት አንድነትና ቁርጠኝነት የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶችና የውስጥ ባንዳዎች እኩይ ዓላማ ሳይሳካ ቀርቷል።

መላው ሕዝባችንና የጸጥታ ኃይላችን የኢትዮጵያን ሕልውና ለማስከበር ላሳያችሁት ተጋድሎና ለከፈላችሁት መስዋዕትነት ያለኝን ክብርና ምስጋና በብልጽግና ፓርቲና በራሴ ስም መግለጽ እወዳለሁ ያሉት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ በቀጣይም ጠላቶቻችን በተለያየ መልኩ መፈተናቸው አይቀርም። ጠላቶቻችን የሚደቅኑብንን ፈተናዎች መሻገር የምንችለው የሀሳብ ልዩነቶችንና የውስጥ ጉዳዮችን በዴሞክራሲ አኳ ኋ ን በጠረጴዛ ዙሪያ በመፍታት ለኢትዮጵያ ሉአላዊነትና የግዛት አንድነት እንዲሁም ለዜጎች ክብር ሳንደራደር በትብብር መሥራት ሲቻል መሆኑን አመልክተዋል።

በተገባደደው 2014 ዓ.ም አገርና ሕዝብን ተጠቃሚ ያደረጉ ሰፋፊ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ስኬቶች መመዝገባቸውን ያስታወሱት አቶ አደም፤ ብልጽግና ፓርቲ በአገራዊ ጉዳዮች ላይ ከሌሎች የፖለቲካ ኃይሎች ጋር በትብብር ለመሥራት ያለውን ቁርጠኝነትም ገልጸዋል

ብልጽግና በ2015 ዓ.ም የፓርቲውን ተቋማዊ አቅም በመገንባትና የውስጠ ፓርቲ አንድነትና ዲሲፕሊንን በማጠናከር መንግሥት የመምራት ሚናውን በተሻለ መልኩ ለመወጣት ዝግጁ መሆኑንም አረጋግጠው፤መላው ሕዝብም ፓርቲው የኢትዮጵያን ብልጽግና ለማፋጠን በሚያደርገው ጥረት ሁሉ እንደከዚህ ቀደሙ ከጎኑ ሆኖ አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርግ ጥሪ አቅርበዋል።

አዲሱ ዓመት ለመላው ኢትዮጵያውያን የሠላም፣ የጤና፣ የትብብር፣ የአብሮነትና የብልጽግና ዘመን እንዲሆንም መልካም ምኞታቸውን አስተላልፈዋል።

# ኢትዮጵያውያን...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ሆኖ ሰላሙንና ደህንነቱን እንዲያስከብር ለህብረተሰቡ አደራ እላለሁ።

መንግሥት በአንድ በኩል ጠላቶችን እየተከላከለ በሌላ በኩል ደግሞ የልማት ሥራዎችን እያከናወነ ስለሆነ ህዝቡም እንደተለመደው ከመንግሥት ጎን በመቆም ልማታችንን አጠናክረን ማስቀጠል አለብን ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

ብፁዕ ካርዲናል ብርሃነየሱስ ሊቀጳጳሳት ዘካቶሊካውያን የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ፕሬዚዳንት በበኩላቸው፣ “ጊዜን ተጠቀምንበት የምንለው በኃላፊነት መንፈስ ያለፈውንም ሆነ የአሁኑን መቀበል ስንችል ነው። ጊዜን ቆጠብን የሚባለው የሰላም መሳሪያዎች ስንሆን ነው። የሰላም መሳሪያነት የሚጀምረው ደግሞ ከአስተሳሰባችን ነው” ብለዋል። በአዲሱ ዓመት ለሰላምና ለእርቅ ቦታ ተሰጥቶ መወያየትና መነጋገር መልካም ነው ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል።

በዘመን መለወጫ በዓሉ ሁሉም አቅም በፈቀደ መጠን በችግር ላይ የሚገኙ ወገኖችን በማሰብ ፣በመተጋገዝና በመረዳዳት በዓሉን ማሳለፍ እንዳለበትም አስታውቀዋል።

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ምክትል ፕሬዚዳንት ቄስ ዶክተር ኪሮስ ላቀው “እንደግለሰብ፤ እንደቤተሰብ፤ እንደ ሃይማኖት ተቋም እንደ ማህበረሰብም ሆነ እንደአገር ጥንካሬአችንን አይተንና ጠብቀን እንድንቀጥል፤ ደካማ ሆነን በተገኘንበት አቅጣጫ ደግሞ ድካማችንን በማሻሻል ለአዲሱ ዓመት የሁለንተናዊ ልማት አቅም መፍጠር ይገባል” ብለዋል።

በመጨረሻም አዲሱ ዓመት የሰላም፣ የፍቅር፣ የበረከት፣ የዕድገት፣ የሃይማኖትና የልማት ዓመት እንዲሆን ወደ ፈጣሪ በመለመንና በብሩህ ተስፋ እንቀበለው ሲሉ የሃይማኖት አባቶቹ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# «አንድነት ኢትዮጵያ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**



ብሄራዊነትን አስጠብቀው አንድነትን በሚያጎለብቱ በተለያዩ መሪ ተግባራት ተከብረዋል።

ዛሬም ድረስ ዘመን የማይሽራቸው የጥበብ አሻራዎቻችን የብርቱ አንድነታችን ምስክሮች ናቸው ያሉት ሚኒስትሩ፤ የጠንካራ አገር መሠረቱ፤ የጠንካራ የውጭ ግንኙነት መሠረቱ ጠንካራ ውስጣዊ አንድነት እንደሆነ ጠቅሰዋል። “አንድነት ውርሳችን፣ ምግባራችን፣ የመጪው ዘመን ህልማችን እውን ማረጋገጫ ቁልፍ መሳሪያችን ነው” ብለዋል።

በሁሉም ማዕዘናት የሚገኙና ዛሬም ድረስ ዓለም የሚደነቅባቸውን ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ሀብቶችን ከማቆየት ባሻገር የጥቁር ህዝቦች የነጻነት ተምሳሌት ሆኖ መቆየት የተቻለው በኢትዮጵያውያን አንድነት እንደሆነም ሚኒስትሩ ገልጸዋል።

አንድነት የቋንቋ፣ የሃይማኖት፣ የጾታና በሌሎች ልዩነቶች የማይደበዝዝ ህብረ ብሄራዊ ኃይል መሆኑን በወራሪ ጠላቶቻችን የተቀዳጀናቸው አኩሪ የድል ታሪኮቻችን ይመሰክራሉ ነው ያሉት።

የዚህ ዘመን የድል ታሪካችን ውጤት የሆነው የህዳሴ ግድብም አሁናዊ የሆነ የአንድነታችን ማሳያ ነው በማለት፤ ለመጪው ዘመን ጠንካራ፤ ተደማጭና ተጽዕኖ ፈጣሪ አገር ለመገንባት ከምንም በላይ ውስጣዊ አንድነትን ማጠንከር ይገባል ሲሉም ሚኒስትሩ አስገንዝበዋል። ህብረ ብሄራዊ አንድነቱ ጸንቶ እንዲቀጥልም ከሁሉም ብዙ እንደሚጠበቅ ገልጸዋል።

ሚኒስትሩ፤ በየዘመናት የሚያጋጥሙ ፈተናዎችን የተሻገርነው በጠንካራ አንድነት ነው ብለዋል። በአሁኑ ወቅት አንድነታችንን የሚፈታተኑ ሃይሎችን እንደ ቀደመው ሁሉ ከፍተኛ መስዋዕትነትን እየከፈለ ለቆመው ሠራዊቱና ልዩ ልዩ የጸጥታ ሀይሉ ምስጋና አቅርበዋል።

ኢትዮጵያ ወደ ከፍታ በምታደርገው ጉዞ የተለያዩ ተጽዕኖዎች እየተሰነዘሩባት እንዳለ በመግለጽ፤ ኢትዮጵያን በሚያደሙ ከሃዲዎች ምክንያት የአንድነት ክንድ የበለጠ እንዲጠነክር የሚጠይቅ ጊዜ ላይ እንገኛለን ብለዋል። ጠንካራ አንድነት ለመገንባት ከመቼውም ጊዜ በላይ መረባረብ እንደሚገባም አመላክተዋል።

የመከላከያ ሚኒስትሩ ዶክተር አብርሃም በላይ በበኩላቸው፤ ያለፉት አራት ዓመታት በፈተና ቢታለፉም፤ ሠራዊቱ ከፓርቲ መሳሪያነቱ ወጥቶ የአገርና የህዝብ መከታ ሆኖ እንዲገነባ መደረጉን አንስተዋል። ሠራዊቱ በፈተና ሳይበገር ሉዓላዊነትን በማስከበር አንጸባራቂ ድሎችን እያንጸባረቀ ይገኛል ብለዋል። ህዝቡ ከዘመን ዘመን እንዲሻገር እያደረገ መሆኑን በመጠቆም ለመላው ኢትዮጵያውያን የእንኳን አደረሳችሁ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።

# «አዲሱን ዘመን...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ወደፊት እንድንጓዝ ስንቅ የሚሆኑ ድሎች የተመዘገቡበትም ዓመት ነበር። ተደራጅተው በዘመቱብን ቁጥር ተደራጅተን መመከት እንደምንችል ያሳየንበት፣ የማዕቀብ ውርጅብኞችን መሻገር ወደሚያስችሉ መንገዶች ጥርሳችንን ነክሰን የገባንበት፣ በምግብ ራስን የመቻል ጉዟችን ተስፋ የፈነጠቀበት፣ ሉአላዊነታችን እንዲታፈር የሚያስችል ዐቅም እንድናደረጅ እድል የተፈጠረበት ጊዜ ስለነበር፣ ዓመቱን በምሬት ብቻ ሳይሆን በምስጋናም ጭምር እንድናስበው ያደርገናል።

አዲስ ዓመት ማክበር ትርጉም የሚኖረው በጊዜ ውስጥ ለማለፍ የምንችል ከሆነ ነው። ጊዜ ይዞን ለሚሄድ ሰዎች አዲስ ዓመት የሚባል ነገር የለም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በየዘመኑ ትናንት ያልታሰበና ያልተደረገ አዲስ ዐሻራ በማኖር ታሪክን ፤ አስተሳሰብን ፤ የሰውን ልጅ የአኗኗር ዘይቤ መቀየር ያስፈልጋል ብለዋል።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ገለጻ፤ ሀገራችን ጊዜን የሚያሸንፉ ሕያዋን ዜጎች ትፈልጋለች። ዘመኑ እንደ ቁጥሩ አዲስ እንዲሆንላት አዲስ ሥራ በአዲሱ ዘመን የሚሠሩ ዜጎች ያስፈልጓታል። ነባር ችግሮቿን በአዳዲስ መፍትሔዎች የሚተኩ፤ የርሃብ ታሪኳን በብልጽግና፤ የጦርነት ታሪኳን በዘላቂ ሰላም፤ የመከፋፈል ታሪኳን በኅብረ ብሔራዊ አንድነት፤ የግጭት ታሪኳን በወንድምና እኅታማችነት፤ የኋላቀርነት ታሪኳን በዘመናዊነት፤ የሚቀይሩ ሕያዋን ጀግኖች ትፈልጋለች። አዲሱ ዓመት በርግጥም አዲስ እንዲሆንላት አዲስ ታሪክ የሚጽፉላትን ትፈልጋለች።

የዘንድሮ መስከረምና ጥቅምት፣ የካቲትና ግንቦት ካምናው፣ ከካቻምናው፣ ከጥንቱ፣ ከቀደምቱ የተለየ ሆኖ እንዲከበር የሚያደርጉ፣ ዘመን ቀያሪ ልጆች ትፈልጋለች። የዘመን መቀየር አይቀሬ ነገር ነው። ዘመንን ራሱን መቀየር ግን የጀግኖች ሥራ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ አረንጓዴ ዐሻራ፣ የበጋ ስንዴ፣ የቱሪዝም ሀብቶቻችንን በራሳችን ዐቅም የመጠቀም ጅማሮ፣ ሀገራዊ ችግሮቻችንን በውይይት የመፍታት ውጥን፣ ከውጭ ተጽዕኖ ለመላቀቅ በገቢ ራስን የመቻል እንቅስቃሴ፣ የዚሁ አካል እንደነበሩ አውስተዋል።

በአዲሱ ዓመት አገልግሎት አሰጣጥን ከሌቦች በማጽዳት፣ የፍትሕ ሥርዓቱን ውጤታማ በማድረግ፣ የኑሮ ውድነትን ጫና በመቀነስ፣ የአምራች ዘርፉን ድርሻ በማሳደግ፣ ኅብረ ብሔራዊ አንድነትን በማጠናከር፣ ግጭቶችን በማስወገድ ግብርናን ይበልጥ ማዘመን እንደሚገባ አመልክተው፤ እነዚህን ሁሉ ለማሳካትም ኢትዮጵያ ጀግኖች ትፈልጋለች ብለዋል።

ሰው የመሆናችን ልዩነት የሚፈጠረው የራሳችንን አዲስ ዓመት ራሳችን ስንፈጥረው ነው። ያን ማድረግ የምንችለው ደግሞ አዲስ ሥራ በመሥራት ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ በአዲሱ ዓመት ለኢትዮጵያችን አዳዲስና ዘመናዊ አሠራሮች፣ መንገዶች፣ ዕይታዎች፣ ዐሻራዎች፣ ምርቶች፣ የኪነ ጥበብ ሥራዎች፣ ፕሮጀክቶችና የግብርና ዘይቤዎች በማምጣት ዘመኑን አዲስ እንድናደርገው ሲሉ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል።በድጋሚ ዘመኑን በአዲስ ሥራ አዲስ አድርገነው አዲስ ዓመት እንዲሆንል እመኛለሁ ብለዋል።

# ‹‹ሀገራችንን ልዩ ከሚያደርጓት መገለጫዎች አንዱ የዘመን አቆጣጠር ስልቷ ነው››

*- መምህር ሔኖክ ያሬድ ፈንታ*

**ጽጌረዳ ጫንያለው**



የአባታቸው ደቀመዝሙር ናቸው ።የ11ኛ ክፍል ተማሪ እያሉ ነበር በአጋጣሚ ከባሕረ ሐሳብ ጋር የተዋወቁት ።መማር የጀመሩት ።በዚህ ቀን ትፈተናላችሁ ሲባል ዕለቱን ለማወቅና ለመዘጋጀት አስበው ከቤት ውስጥ የነበረውን ተንጠልጣይ ካሌንደር ሲፈልጉ በቀላሉ ማግኘት አልቻሉም ።ስለዚህም በመፈለግ ጊዜያቸውን እንዳይፈጁ የፈለጉት ሐሳበ አቡሻህርን ጨምሮ የተለያዩ ሐሳቦችን የያዘው የባሕረ ሐሳብ መምህሩ አባታቸው ሊቀ ሊቃውንት ያሬድ ፈንታ ከወንበራቸው ሥር ወረቀትና ብዕር ይዘው እንዲቀመጡ አደረጓቸው ።

ማወቅ ያለባቸውን ዋና ዋና ነጥቦችን ጨምሮ የማንኛውም ቀን ዕለቱ የሚታወቅበት የስሌት መንገድንም በምሳሌ፡- እያደረጉ አስተማሯቸው ።ጋዜጠኛው መምህር ሔኖክ ያሬድ ፈንታም ትምህርቱን ለመጀመሪያ ችግር መፍቻቸው ብቻ ሳይሆን ለወደፊቱም የመፍትሔ ቁልፋቸው ሊያደርጉት ፈለጉ ።ከአባታቸው የቀሰሙትን እውቀት በቅርባቸው ላሉ ተማሪዎች ማሳወቁንና ክህሎታቸውን ማዳበሩን ተያዙት ።ተማሩና እስከ ሁለተኛ ዲግሪ ድረስም ጥናታዊ ሥራዎችን ከወኑበት፤ አስተማሩበትም ።

አሁንም የተለያዩ ጥናታዊ ጽሑፎችን ዩኒቨርሲቲዎችን ጨምሮ በተለያዩ መድረኮች ላይ አቅርበውበታል ።ስለ ኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ምንነትና ፎክሎራዊ ገጽታ ለቱሪስት አስጎብኚዎች፣ ለባህልና ቱሪዝም ባለሙያዎች በተለያዩ ቦታዎችም እየተጋበዙ ሥልጠና ሰጥተውበታል ።እያስተማሩም ነው ።ይህ የዘመን አቆጣጠር በአገራችንና በዓለም ደረጃ እንዴት ይታያልና መሰል ጥያቄዎችን በማንሳት ከሕይወት ልምዳቸው ጋር በማድረግ ልናነጋግራቸው ወደናልና ተጋበዙልን ።

**አዲስ ዘመን፡- የእርስዎን የሕይወት ተሞክሮ ስናነሳ አባትዎን ሳይጠቅሱ ማለፍ በፍጹም አይቻልም ።የዛሬውን መምህር የሠሩት እርሳቸው ናቸው ይባላል ።**

**መምህር ሔኖክ፡-** የሥጋም የቀለምም አባቴ ከአካዳሚያው ትምህርት አስቀድሞ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ልዩ ልዩ የአብነት ትምህርቶችን ተምረዋል፣ ቀጽለዋል ።በርካታ መጻሕፍትን አዘጋጅተዋል ።ከነዚህም መካከል የግእዝ ቋንቋ መማሪያ (ፍኖተ ግእዝ ዘመናዊ)፣ የእንግሊዝኛና የአማርኛ ሰዋስውን የሚያስተምረው የንግግር ሥርዓቶችና አገባቦች፣ የዘርዐ ያዕቆብና የወልደ ሕይወት ሐተታዎች ትርጉምና ባሕረ ሐሳብ የቀመርና የሥነ ፈለክ ምሥጢር ይገኙበታል ።

ባሕረ ሐሳብን በጥልቀት ያጠኑ፣ ኢትዮጵያ ስምንት ዓመት ጨምራ የምትቆጥርበትና ወደኋላ የሚቀር ዘመን እንደሌላት ለመጀመሪያ ጊዜ ይፋ ያደረጉት እሳቸው ናቸው።አሁንም ከእሳቸው ወንበር እየቀጸልሁ ነው።የረቀቀውን የዘመን መቁጠሪያ ጥበብ በመማሬም ብዙዎችን አስተምሬያለሁ።ከዲፕሎማ እስከ ሁለተኛ ዲግሪ ድረስ ስማር የተለያዩ የትምህርት መስኮችን ቃኝቻለሁ።ሁሉንም ግን ከባሕረ ሐሳብ ጋር እንዳገናኛቸውና የበለጠ እውቀት እንድጨብጥባቸው አድርጎኛል ።

በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከተማሪነቴ ጀምሮ እንድጽፍና የጽሑፍ ጥበብን እንድረዳም ከአባቴ የተሰጠኝ ትምህርት በብዙ መልኩ አግዞኛል ።ተነባቢ በነበረው የየካቲት መጽሔት የውጭ ጸሐፊ ሆኜ እስከ መሥራት ደርሻለሁ ።ቅድስት ሥላሴ ዩኒቨርሲቲን ጨምሮ በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ከማስተማር ባለፈ ባሕረ ሐሳቡን አስመልክቶ ጥናታዊ ጽሑፎችን ለማቅረብ ችያለሁ ።እየሠራሁበት ባለው ሪፖርተር ጋዜጣ ላይ በተለይ ትውፊትና ዘመንን በተመለከተ ጥናት ተኮር መጣጥፎችን ለማዘጋጀት ባሕረ ሐሳቡ ትልቅ አቅም ፈጥሮልኛል ።

**አዲስ ዘመን፡- የዘመን አቆጣጠር እንዴት ይገለጻል፣ የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ከሌሎች የተለየ የሆነበት ምክንያት ምንድነው?**

**መምህር ሔኖክ ፡-** የዘመን አቆጣጠርን ሐሳበ ዘመን እንለዋለን ።በቁሙ ሲፈታ የዘመን ቁጥር፣ ዕድሜ ማለት ነው ።በሌላ አገላለጽ ‹‹ባሕረ ሐሳብ›› ይባላል። እርሱም ቁጥር ያለው ዘመን ተብሎ ይፈታል ።ሐሳበ ዘመን ‹‹ካሌንደር›› ተብሎም ይጠራል ።በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥም ይገኛል ።አገራችንን ልዩ ከሚያደርጓት መገለጫዎች አንዱ የዘመን አቆጣጠር ስልቷ ነው። የዓመት ቁጥር ልኬት መባቻውን መስከረም 1 ቀን በማድረግ በፀሐይ 365 ከሩብ ቀን ይዘልቃል ።

አመዳደቡም 12ቱ ወር እያንዳንዱ ወር 30 ቀን፣ እንዲሁም ጳጉሜን ተብለው የሚታወቁ ሦስቱን ዓመት 5 በአራተኛ ዓመት 6 ቀኖችን የያዘ ነው ።ይህ የ13 ወራት አቆጣጠር በኛ ብቻ ሳይሆን በግብፅ ኮፕቲክም እየተሠራበት ይገኛል። ከሌሎቹ አቆጣጠሮች መካከል በዓለም አገልግሎት እየሰጠ ያለው በዘልማድ ‹‹የአውሮፓውያን አቆጣጠር›› የሚባለው ጎርጎርዮሳዊው ቀመር፣ ከርሱ በፊት የነበረው የጁሊየስ ቀመርን ጨምሮ ዓመቱን በ12 ወሮች ሲመድቡ የእያንዳንዱ ወር የቀን ብዛት 28፣ 30 እና 31 በማድረግ ይዘምታሉ ።የዓመቱ መጀመሪያቸው ጃንዋሪ (ታኅሣሥ/ጥር) ላይ ነው ።

እዚህ ላይ የሚነሣው ነጥብ አንዳንዶች በጽሑፍ ጭምር ሲገልጹ የኛን አቆጣጠር ‹‹የጁሊያን ካሌንደር›› ይላሉ ።ይህ ስሕተት ነው ።የጁሊያን አቆጣጠር መባቻው ጃንዋሪ መካተቻው ዲሴምበር ነው ።በየአራት ዓመቱ አንድ ቀን የሚጨምሩት በሁለተኛው ወራቸው 28 የነበረችው ፌብሪዋሪን 29 በማድረግ ነው ።በወር አደረጃጀት፣ በቀን መደብ፣ ባመት መባቻ አንገናኝም። የመሬት ዑደት 365.25 ቀን ነው ማለትን ብቻ እንጋራለን። አቆጣጠራችን ከግብፅ/ኮፕት ጋር ነው የሚመሳሰለው ።

**አዲስ ዘመን፡- ስለ ሐሳበ ዘመን ዓይነቶች ቢያብራሩልን?**

**መምህር ሔኖክ፡-** የዘመን አቆጣጠር መለኪያዎች ቀን፣ ወርና ዓመት ናቸው ። ይህም በመሬት፣ በፀሐይና በጨረቃ እንቅስቃሴዎች አማካይነት የሚገኝ ነው። ቀን የሚለካው መሬት በራስዋ ዛቢያ (መስመር) ላይ በምታደርገው ዑደት (ዙረት) ነው ።የጨረቃ ወር ሲባል ጨረቃዋ በ29 ወይም በ30 ቀኖች ውስጥ እያፈራረቀች ዙረትዋን የምትፈጽምበት ጊዜ ነው። ዓመት የሚለካው መሬት በፀሐይ ዙሪያ ዞራ ወደ ነበረችበት ለመመለስ በሚፈጅባት ጊዜ ነው ።በዚህም ጉዞዋ አማካይነት አራቱ ወቅቶች ማለትም ክረምት (ከሰኔ 26 እስከ መስከረም 25)፣ መፀው (ከመስከረም 26 እስከ ታኅሣሥ 25)፣ በጋ (ከታኅሣሥ 26 እስከ መጋቢት 25)፣ ፀደይ/በልግ (ከመጋቢት 26 ሰኔ 25) የተባሉት ይፈራረቃሉ ።

ሌሎች ዓውዶች የሚባሉ የዘመን መስፈሪያዎችም አሉ ። ዞረው የሚመጡት ዓውዶች ማለትም ዓውደ ዕለት ከእሑድ እስከ ቅዳሜ ያሉት 7 ቀኖች፣ ዓውደ ወርኅ በጨረቃ 29/30 ቀን፣ በፀሐይ ዘወትር 30 ቀን፣ ዓውደ ዓመት በጨረቃ 354 ቀን፣ በፀሐይ 365 ቀን፣ ዓውደ ጳጉሜን 4 ዓመት፣ ዓውደ አበቅቴ 19 ዓመት፣ ዓውደ ፀሐይ 28 ዓመት፣ ዓውደ ማኅተም 76 ዓመት፣ ዓውደ ቀመር 532 ዓመት ናቸው ።ከጠቀስናቸው የብርሃናት መለኪያ አንፃር የሐሳበ ዘመን ዓይነቶች ሦስት ናቸው ። እነርሱም የፀሐይ፣ የጨረቃ የፀሐይና የጨረቃ ጥምር አቆጣጠሮች ተብለው ይጠራሉ ።

ፀሐያዊው አቆጣጠር (ባለ 365/6 ቀን) በመደበኛነት እያገለገለ የሚገኝ ሲሆን የኢትዮጵያ አቆጣጠር፣ የአውሮፓውያን አቆጣጠር ወዘተ ያሉትን ይመለከታል ።የጨረቃው አቆጣጠር (ባለ 354 ቀን) በተለይ በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ በዓመተ ሒጅራ ይታወቃል ።የፀሐይና የጨረቃ ጥምር አቆጣጠር ከአይሁድ ጋር ይያያዛል ።አይሁድ ወራቸውን በጨረቃ፣ ዓመታቸውን በፀሐይ ይቆጥራሉና ።የቤተ ክርስቲያን የዘመን አቆጣጠርም ይጋራዋል ።

ሁለቱን የብርሃን መንገዶች አቆጣጠርን ይከተላል። የልደት በዓልን የሚመስሉ በቋሚ ቀን የሚውሉት ፀሐይን ብቻ ሲከተሉ፤ ትንሣኤ (ፋሲካ) እና ከርሱ ጋር ተያያዥ የሚሆኑት በየዓመቱ የሚውሉበት ቀን የሚለዋወጠው ደግሞ የሁለቱን ፀሐይና ጨረቃ አቆጣጠር ይጠቀማሉ ።የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በተለይ መስከረም 1ን ርዕሰ ዓውደ ዓመት ቅዱስ ዮሐንስ ትለዋለች ።በዘመን መለወጫ ቀን በተለያዩ ታሪካዊ የዓመት መነሻዎች በሦስቱ መንገዶች በማስላት የዘመኑን ተዘዋዋሪ አጽዋማትና በዓላትን ታውጅበታለች ።

ከመደበኛው የዓመተ ምሕረት አቆጣጠሯ (ዓመተ ሥጋዌም ይባላል) በተጨማሪ በተለያዩ ታሪካዊ መነሻዎችም ዘመኑን ታሰላለች ።አንደኛው ዓመተ ዓለም ነው ።ዓለም ከተፈጠረበት ከክርስቶስ ልደት 5500 ዓመት በፊት አንስቶ ነው የሚቆጠረው ።በዚህም መሠረት ዛሬ በጀመርነው በ2015 ዓ.ም ዘመኑ 7515 ዓመተ ዓለም ይሆናል ።ይህም ዘመኑ ስምንተኛው ሺህ ውስጥ እንዳለን ያሳየናል ።

ሌላኛው ጥምር አቆጣጠር ሲሆን፤ በዚህ አቆጣጠር በዛሬው መስከረም 1 ቀን በፀሐይና ጨረቃ ጥምር አቆጣጠር የኢትዮጵያ 2023ን ጀምረናል ።ይህ ጥምር አቆጣጠር ትንሣኤን ይዘው በሚንቀሳቀሱና ልደትን ይዘው በማይንቀሳቀሱ በዓላትና አጽዋማት መካከል ያለውን ልዩነት ለማወቅ ይረዳል። በፀሐይ መስከረም 1 ቀን በጨረቃ ‹‹መስከረም 15›› መሆኑን፣ በሒጅራ ሠፈር 15ቀን 1444፣ በአይሁድ ኢሉል 15 ቀን 5782 መሆኑን ዕለታቱ በሦስቱም ሃይማኖቶች በጨረቃ አቆጣጠር ተመሳሳይነት ያረጋገጥነው በ2023 አቆጣጠራችን ነው ።እዚህ ላይ የዕለት የ‹‹24 ሰዓት›› መነሻ ሁለት ዓይነቶች መኖራቸውን ማስታወስ ይገባል ።

አንደኛው ከኛ አንፃር መደበኛው ፀሐያዊ ዕለት ‹‹ሲቪል ዴይ›› የሚባለውና ጠዋት 12 ሰዓት የሚጀመረው ሲሆን፣ ከሥርዓተ አምልኮ ጋር የሚያያዘው ማታ 12 ሰዓት የሚጀመረው ‹‹ዕለተ ሊጡርጊያ›› (ሊተርጂካል ዴይ) ሌላው ነው ።በሌላ በኩል እያንዳንዱ ዓመት በአራቱ ወንጌላውያን እንደ ቅደም ተከተላቸው ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ (ባመቱ መጨረሻ ጳጉሜን 6 የምትሆንበት) እና ዮሐንስ ተብለው ተሰይመዋል። ለምሳሌ የያዝነው 2015 ዘመነ ሉቃስ የሚያበቃው በ366ኛው ቀን ላይ ጳጉሜን 6 ነው ።

**አዲስ ዘመን፡- ስለ አዲስ ዓመት ከማውራታችን በፊት እስቲ ልዩ ስለሆነችዋ ጳጉሜን ይንገሩን?**

**መምህር ሔኖክ፡-** ጳጉሜን ከነሐሴ ወር መጨረሻ አዲስ ዓመት ከሚጀመርበት መስከረም አስቀድመው የሚገኙ ዕለታትን ያቀፈች ናት ።ጳጉሜን ተጨማሪ ተብሎ ይተረጐማል። የ12ቱ ወራት 360 ቀኖች ብቻ ዓመቱን ሙሉ አያደርጉትም ።የሚሞላው የመጨረሻዎቹ የጳጉሜን ቀናት 5 ቀኖች (በአራት ዓመት 6) ሲመጡ ነው ። ንዑስ ወሩ ተጨማሪ የሚል ትርጉም ያገኘው በ12 ወራት ላይ የሚጨመር ስለሆነ ሲሆን፣ በሌላ በኩልም ከወሮች ዑደት ተርፎ ስለተገኘም ትርፍ ይባላል ።

ጳጉሜን ከዓመት ማጠቃለያ ባለፈ፣ እንደ ዘመን መነሻም የሚታሰብበት ልዩ መንገድ ሊቃውንቱ አላቸው። ‹‹ጳጉሜን የመጨረሻ አትምሰልህ የመጀመሪያ እንጂ›› ይሉታል ።ጳጉሜን እንደ አሮጌ ዓመት መዝጊያና የአዲስ ዓመት መጀመሪያ አድርጎ በማሰብም ሰዎች ራሳቸውን የሚገመግሙበትና ለመጪው አዲስ ዓመት ደግሞ እግዚአብሔር ምሕረቱን ረድኤቱን እንዲያበዛላቸው እየለመኑ ለበለጠ ሥራ ራሳቸውን የሚያዘጋጁበት ጊዜ ነው ።

**አዲስ ዘመን፡- መስከረም ስምን የአዲስ ዓመት መነሻ እንዲሆን ተመረጠ ይላሉ?**

**መምህር ሔኖክ፡-** በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታችን ስለ አማርኛ ግጥም ስንማር ከማስታውሳቸው አንዱ ስለ የዓመቱ ወራት የቀረበውን ነው ።

**‹‹ጨለማው ሲጠፋ ዝናቡ ሲያቆም**<br>
**ያ የለውጥ ወራት መጣ መስከረም**<br>
**ሰዎች ይነሣሉ ሲሠሩ ታጥቀው**<br>
**መስከረም ነውና ብርሃን ሰጪው››** እያለ ዓመቱን ይዘልቃል ።ስለሆነም መስከረም ከባዱ ክረምት ቀዝቃዛ የሚልበት ደመራ ከተለኮሰ በኋላ መሰስ ብሎ

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

የሚወጣበት፣ ምድሪቱ በአደይ አበባ የምታሸበርቅበት ነው ።‹‹መስከረም መስከረም የወራቱ ጌታ አበቦች ተመኙ ካንቺ ጋር ጨዋታ›› መባሉም ለዚህ ነው ። ሰ እና ዘ ተወራራሽ ናቸውና መስከረም ‹‹መዝከረም››ም ይባላል ።መዘከረ ዓም (የዓመት መታወሻ) ተብሎ ዘመን ይሰላበታል፤ በዓላትና አጽዋማት ይታወጅበታል ።በእርግጥ መስከረምን እንደኛ የአዲስ ዓመት መግቢያ የምታደርገው የግብፅዋ ኮፕቲክ ናት ።ከመስከረም ጋር በሚገናኘው ሴብቴምበር ዓመታቸውን የሚጀምሩት ቢዛንታይኖች እነ ግሪክ ኦርቶዶክስ ናቸው ።በኛ ነሐሴ 26 ላይ በዋለው ሴብቴምበር 1 ቀን አክብረዋል ።

እስራኤሎች ‹‹ሮሽ ሃሻናህ›› የዓመት መጀመሪያ/ ርዕሰ ዓመት የሚሉት የጨረቃ ጥቅምት 1 ቀን በአብዛኛው በመስከረም ወር ውስጥ ይውላል ። ዓለም በዚህ ወር ተፈጥሮበታል ብለው ያምኑበታል ። ሌላው መስከረም ወር እንደ መጋቢት ቀንና ሌሊቱ በ25ኛው ቀን ላይ እኩል 12፣ 12 ሰዓት የሚሆንበት ነው ።በ13 ወራት መደብ በ366 ቀናት የሚከበሩ የቅዱሳንና የነገሥታት እንዲሁም የዓለሙን ታሪክ በያዘው በጥንታዊው መጽሐፍ ስንክሳር፣ የዓመቱ መጀመሪያ መስከረምን ስለሆነ ይተነትነዋል።

‹‹የተባረከ የመስከረም ወር የግብፅ፣ የኢትዮጵያና የኑቢያ ዓመታት ወሮች ራስ ነው። የቀኑ ሰዓትም ከሌሊቱ ሰዓት የተስተካከለ አሥራ ሁለት ነው። ከዚህ በኋላ እያነሰ ይሄዳል ።›› ይህም የቀን እኩል ወይም ዕሪና ከክረምት ቀጥሎ በሚመጣው የአበባና የነፋስ ወቅት በመፀው፣ ‹‹የመፀው ዕሪና›› ተብሏል። ይህ ቀን ከዘመነ አክሱም ጀምሮ ክረምቱ ማለፉን አበቦች መፍካታቸውን ለማመልከት ‹‹ተቀፀል ጽጌ›› (አበባን ተቀዳጅ) እየተባለ በየዓመቱ እስከ 15ኛው ምዕት ዓመት ሲከበር ቆይቷል። ከዚያ ወዲህ ግማደ መስቀሉ ከመጣበት ጊዜ አንሥቶ ግን በመስከረም 10 ቀን እየተከበረ ይገኛል ።

**አዲስ ዘመን፡- በአንድ በኩል ኢዮሃ አበባዬ ተያይዞም ዕንቁጣጣሽ ይባላል፤ ምንድን ይገልጻል?**

**መምህር ሔኖክ፡-** ‹‹ኢዮሃ አበባዬ-መስከረም ጠባዬ›› ዘመን በተለወጠ ቁጥር የሚያስተጋባ ነው። በመጻሕፍት እንደተጠቀሰው፣ ኢዮሃ አበባዬ የደስታ ቃል ነው ።ወንዶች የደመራ ዕለት እየዘፈኑ ድምፉን የሚዞሩበት የአበባ ዘፈን ነው ።ሰኔ ግም ብሎ፣ ያምሌን ጨለማ አልፎ፣ የነሐሴን ጎርፍ ሙላትን በእኝኝ ተሻግሮና ተንተርሶ በጠንካራው ዝናብ (ውኃ) ምክንያት ብቅ የምትለዋ ያደይ አበባ ናትና፤ ውኃ ያደረገውን ታምር፣ ያስበቀለውን አበባ አደያዊን ተመልከት ለማለት ‹‹ኢዮሃ አበባዬ መስከረም ጠባዬ›› ይባላል ።

ወደ ዕንቁጣጣሽ ስንመጣ ከትውፊት የሚቀዱ አገላለጾች አሉ ። ከአዲስ ዓመት ዋዜማ ጀምሮ በተለይም በወርኃ መስከረም መሬቷ በአደይ አበባ አሸብርቃ ስለምትታይና በተለይም ዕንቁ የመሰለ አበባ ስለምታወጣ መሬቷን ዕንቁጣጣሽ፣ ‹‹ዕንቁ የመሰለ አበባ አስገኘሽ›› ለማለት ዕንቁጣጣሽ ተብላለች ።አያይዘው አቧራ፣ ቡላ የነበረው መሬት በዝናቡ ኃይል ለምልሞ ተመልከቱኝ፣ ተመልከቱኝ የምትል ያሸበረቀች፣ አበባ የተንቆጠቆጠች ሆነች የሚል ለዕንቁጣጣሽ ስያሜ መነሻ ሊሆን እንደሚችል ይጠቁማሉ ።

በሌላ ተረክም ዕንቁጣጣሽን ንግሥተ ሳባ ኢየሩሳሌም ሄዳ ጉብኝቷን ፈጽማ ስትመለስ ንጉሥ ሰሎሞን ብዙ ዕንቁ ለጣጣሽ ‹‹ለችግርሽ›› ይሁን ብሎ መታሰቢያ ከሰጣት ጋር ተያይዞም ይነገራል ።ከልዩ ልዩ ተረኮች መካከል እነ አፈ ሊቅ አክሊሉ ገብረኪሮስ፣ አለቃ ነቢየ ልዑል በተውልን ማስታወሻ ላይ እንደተገለጸው፣ ማክዳ የምትባለው ንግሥተ ሳባ አንድ ዓመት ያህል ቆይታ ከመናገሻ ከተማዋ በገባች ጊዜ ወንዱ በሆታ ሴቱ በዕልልታ ሲቀበላት፣ ሕፃናቱ ደግሞ አበባ፣ ለምለም ቅጠል ይዘው ነበር የተቀበሏት ።

‹‹ሰሎሞን ዕንቁ ለጣጣሽ ሰጠሽ፣ በዓመትሽ እንኳን ደህና መጣሽ፤›› እያሉ ስለተቀበሏት ልምድ ሆኖ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ መጥቷል ።ከጊዜ ብዛት ዕንቁ ለጣጣሽ የሚለውን ‹ለ›ን በመግደፍ ዕንቁጣጣሽ ሆነ ይላሉ ። በዕለቱ ልጆች በየቤቱ እየሄዱ ‹‹ዕንቁጣጣሽ በያመቱ ያምጣሽ›› እያሉ አበባ ያበረክታሉ፣ ሥዕል ይሰጣሉ ።እዚች ላይ በዕንቁጣጣሽ ዋዜማ አዲሱ ዓመት መድረሱን ስለሚያበስረው እንግጫ ማንሣት ይገባል ።እንግጫ የሳር ዓይነት ነው ።በአዲስ ዓመት ዋዜማ ልጃገረዶች መስክ ወርደው የሚነቅሉት ነው። የዕንቁጣጣሽ ብሥራት ነጋሪ ነው ።በአንድ የማይዳሰሱ ቅርሶች ድርሳን ላይ እንዳነበብሁት፣ በዘመን መለወጫ ዋዜማ እንግጫ ሳር በልጆች እየተነቀለ እንደቋጨራ እየተጎነጎነ ጣራ ላይ ተወርውሮ የድርና ጠዋት ላይ ለዘመን መለወጫ መስከረም 1 ቀን እየተጎነጎነ ራስ ላይ፣ ቡሃቃ አንገት ላይና ሌማት ክዳን ላይ ይታሰራል ።

ቡሃቃ እና ሌማት ላይ የመታሰሩ ምልክትነት ለረድኤትና ለበረከት ሲባል የሚደረግ ነው ።ራስ ላይ የታሰረው ደግሞ ለመስቀል በዓል ተቀምጦ ይቆይና ደመራው ላይ ይታሰርና እንዲቃጠል ይደረጋል ።ለራስ ምታትና ለጤንነት ሲባል በማኅበረሰቡ የሚከወን ነው ። እንግጫ ከአዲስ ዓመት ማብሰሪያ በተጨማሪ የመተጫጫ በዓልም ጭምር ነው ።

**አዲስ ዘመን - በዓለም ላይ ኢትዮጵያን ጨምሮ የራሳቸው ዘመን አቆጣጠር ያላቸው አገራት ምን ያህል ናቸው?**

**መምህር ሔኖክ፡-** በርካታ አገሮችና ሃይማኖቶች ቀኖችን፣ ወሮችን እና ዓመቶችን የሚቆጥሩበት የየራሳቸው የዘመን አቆጣጠር ወይም ካሌንደር አላቸው ።በአገራችንም እንደዚሁ። አቆጣጠሮቹም በሦስት ዓበይት የካሌንደር ዓይነቶች ይገለጻሉ። እነርሱም የጨረቃ፣ የፀሐይ እና የጨረቃና ፀሐይ ጥምር አቆጣጠሮች ናቸው ።ባንድ የዳሰሳ መረጃ ላይ እንደተጠቀሰው በዓለም ዙሪያ ከ40 በላይ ካሌንደሮች በአገልግሎት ላይ ይገኛሉ ።በዓለም ካርታ አስደግፎ የቀረበው መረጃ ከአፍሪካ ኢትዮጵያና ግብፅን፤ ከአውሮፓና እስያ ሮም (ጣሊያን)፣ ግሪክ፣ ባቢሎን ፋርስ (ፐርሺያ)፣ ቻይና፤ ከማዕከላዊ አሜሪካ ማያን እና አዝቴክ ተጠቅሰዋል ።

**አዲስ ዘመን፡- አንዲት አገር የራሷ የዘመን አቆጣጠር አላት ማለት የሚያስገኘው ጥቅም ምንድን ነው፤ ከሥልጣኔ አንፃርስ እንዴት ይታያል?**

**መምህር ሔኖክ ፡-** በርካታ ጥቅም አለው።የመጀመሪያው በሕይወት ለመኖር የሚያስችሉ መሠረታዊ ነገሮችን ለማሟላት አራቱ ወቅቶችን (ክረምትና መፀው፣ በጋና ፀደይ) የሚገቡበትን ማወቅ አንዱ ግዴታ ነው ። ዝናቡ መቼ እንደሚመጣ፣ መቼ እንደሚተከልና መቼ እንደሚሰበሰብ ለማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው ። ብርሃናት የተፈጠሩት ለምልክቶች፣ ለዘመኖች፣ ለዕለታትና ለዓመታት ነው ።ሁሉም የቀን መቁጠሪያዎች በጊዜ ሒደት ለመቁጠር በሚረዱን በሦስት ዑደቶች ወይም ተደጋጋሚ ክስተቶች ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውን አስቀድመን አንሥተናል ። እነዚህም ቀኑ - ከፀሐይ መውጫ እስከ ፀሐይ መውጫ ወይም ፀሐይ ከጠለቀች እስከ ፀሐይ መግቢያ፣ ወር-ከሙሉ ጨረቃ እስከ ቀጣዩ ሙሉ ጨረቃ (ወይም ከአዲስ ጨረቃ እስከ ቀጣዩ አዲስ ጨረቃ) እና ዓመት - ከአንዱ በጋ ወደ ቀጣዩ ወይም ከአንዱ ክረምት ወደ ቀጣዩ፣ ወይም ከመፀው እስከ መፀው አሊያም ከፀደይ እስከ ፀደይ ናቸው።

ቀኑ ረዥም ሌሊቱ አጭር፣ እንዲሁም ሌሊቱ ረዥም ቀኑ አጭር የሚሆንበት ገጽታውን ከሥነ ፈለክ አንፃር በመመርመር የተገኘ ነው ። የራስ የዘመን አቆጣጠር መኖር ከአየር ንብረት ጋር ጭምር ራስን አዋሕዶ ለመኳዝ፣ በጀትን ለመመደብ፣ የትምህርት ወቅትን ለማወቅ፣ እቅድ ለመያዝ፣ ለቀዳሽም፣ ለአራሽም ወዘተ እጅግ ጠቃሚ ነው ።ቅዱስ ያሬድ ለዜማው ድርሰቱን ያዘጋጀው በአራቱ ወቅቶች መነሻነት ነው ።መስከረም 1 በክረምት ውስጥ የምትገኝ ያመት መነሻ ናት ።ሰኔ 26 ቀን የገባው ክረምት የሚወጣው መስከረም 25 ቀን ላይ ነው። የስድስተኛው ምዕት ዓመት የነገረ መለኮት ሊቁ፣ ማሕሌታይ ቅዱስ ያሬድ በመጽሐፈ ድጓው ‹‹ኀለፈ ክረምቱ ጸገዩ ጽጌያት ቆመ በረከት!›› - ክረምቱ አለፈ አበቦችም ፈኩ፣ በረከትም ቆመ ይለናል ። እንደ ቅዱስ ያሬድ የዓመት አመዳደብ፣ በውስጡ ልዩ ልዩ ንኡሳን ክፍሎች አሉት ።ከነሱም መካከል የነሐሴ መጨረሻና የጳጉሜን ሳምንት ‹‹ጎሕ፣ ጽባሕ››- ወጋገን፣ ንጋት ይለዋል ።ይህም የአዲስ ዘመን መስከረም የሚጠባበት ጊዜ መድረሱን አመላካች ነው ።

ሌላው ንኡስ ክፍል ከዓመት አውራ መነሻ (ርእሰ ዐውደ ዓመት) መስከረም 1 ቀን እስከ መስከረም 7 (8) ቀን ያለው ‹‹ዮሐንስ›› ሲባል፣ ከመስከረም 9 እስከ 15 ዘመነ ፍሬ ይባላል።‹‹ዮሐንስ›› የሚለው ቃል የተወሰደው በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከሚገኘውና እግዚእ ኢየሱስ ክርስቶስን ካጠመቀው ዮሐንስ ነው ።መስከረም 1 ቀን ቅዱስ ዮሐንስ፣ ዕለተ ዮሐንስ መባሉ በተምሳሌታዊ ፍች የመጣ ነው ።

ከአሮጌው ብሉይ ኪዳን ወደ ሐዲስ ኪዳን፣ ወደ ዓመተ ምሕረት መሸጋገሪያ ላይ የመጣው መንገድ ጠራጊው ዮሐንስ ስለሆነ፤ ባህሉ/ ትውፊቱ ከአሮጌው ዓመት ወደአዲሱ መሸጋገሪያዋን ዕለት፣ መስከረም 1 ቀንን በዘይቤ ዕለተ ዮሐንስ እያለ ይጠራዋል ።ከጥንት



## መስከረም አንድ- በልዩ ልዩ አቆጣጠር

- መስከረም 1፣ 7515 ዓመተ ዓለም (ከአዳም ተነሥቶ የሚቆጥር)
- መስከረም 1፣ 2015 ዓመተ ምሕረት (በፀሐይ)
- መስከረም 1፣ 2023 (በፀሐይና በጨረቃ)
- የጨረቃ መስከረም 15 ቀን 2023 (የክርስትና)
- ሡፈር 14፣ 1444 ዓመተ ሒጅራ (የእስልምና)
- ኢሉል 15፣ 5782 ዓመተ ፍጥረት (የአይሁድ)
- ቲቶ 1፣ 1739 ዓመተ ሰማዕታት (ኮፕቲክ/ግብፅ)
- ኦገስት 29፣ 2022 (በዩሊየሳዊ)
- ሴፕቴምበር 11፣ 2022 (በጎርጎርዮሳዊ)
- ሳህሪቫር 20፣ 1401 (በፋርስ/ኢራን)

እስከ ዛሬ በአገልግሎት ላይ ይገኛል። በባሕረ ሐሳባችን መሠረት አዲሱ ዘመን የሚለወጥበት ንጋት 12 ሰዓት ላይ እንጂ እንደ ምዕራባውያን እኩለ ሌሊት (6 ሰዓት) አይደለም ።

**አዲስ ዘመን፡- ብዙ ጊዜ መስከረምና ጥቅምትን ‹‹ፀደይ›› ሲባል እንሰማለን ነውን?**

**መምህር ሔኖክ፡-** ስሕተት ነው ። ፀደይ በልግ ሲሆን፣ ከመጋቢት እስከ ሰኔ ይቆያል ።የአደይ አበባና የነፋሱ ወቅት መፀው ሲሆን፤ ፍቺው አበባ ነው። በአውሮፓ በጋ ሲሆን፣ በኛ ክረምት ነው ። ለእነሱ ፀደይ ሲሆን ደግሞ ለኛ መፀው ይሆናል ። ሰው ያለ አጥቢያው ወቅቱን ማዘዋወሩ ነው ያስቸገረን ። በተለይ በአብዛኛው የጥበብ ሰዎች ።ስለዚህ በዚህ ተስተካክሎ መታየት አለበት ።

**አዲስ ዘመን፡- መስከረም ለኢትዮጵያውያን ምን ትርጉም አለው፤ የተለያዩ እምነቶች ቢኖሩም ሁሉም በደስታ የሚያከብሩትና ተስፋ የሚጥሉበት ወር ነው። ለመሆኑ እንድ ያደረጋቸው ምንድነው ይላሉ?**

**መምህር ሔኖክ፡-** በፀሐይ ላይ የተመሠረተው የዓመት አቆጣጠር አራቱን ወቅቶች የሚያስገኝልን ነው። ለኛ መስከረም የወራቱ ጌታ የአበቦቹ እመቤት ናት። መምህራኑ እንደሚገልጹት ክረምት የሚያልፍበት፣ ዝናብ የሚቆምበት ፀሐይ የምትኀላበት ወንዞች ንጹሕና የጠራ ውኃ የሚጎርፉበት፣ ምንጮች የሚፈልቁበት የተዘሩት ማሽት የሚጀምሩበት፣ ሜዳዎችና ተራራዎች ሸለቆዎችም በአበባ የሚያሸበርቁበት ነው። ‹‹የመስቀል ወፍ›› የምትባለው የመስከረሟ ወፍ ነባር ቀለሟን ለውጣ የምትታይበትም ነው ።‹‹የመስቀል ወፍና አደይ አበባ ቀጠሮ እንዳላቸው ማን ያውቋል?›› አይደል ያሉት ታላቁ ባለቅኔ መንግሥቱ ለማ ።

መስከረምን የአዲስ ዘመን መባቻ እንዲሆን የተተለመበት ዓቢዩ ምክንያት ከቀድሞው ዘመን አንፃር ሲታይ ታቹ ውኃ፣ ላዩም ውኃ ሆኖ ወገን ከወገኑ ዘመድ ከዘመዱ አለያይቶ የነበረው የክረምቱ ሦስት ወራት አልፎ፣ የተለያዩት የሚገናኙበት የራቁት የሚቀርቡበት በመሆኑ ነው ።ትምህርት ቤት ሰኔ 30 ተዘግቶ በመስቀል ደመራ ማግስት መስከረም 18 ቀን ይከፈት የነበረው ለዚህ ነው ።ስለዚህም እነዚህ ጉዳዮች ሁሉንም ኢትዮጵያውያን ያገናኟቸዋል ።

**አዲስ ዘመን- አዲስ ዘመን ሲመጣ ሰዎች ያቅዳሉ ።ይሁን እንጂ እቅዶቹ ወደ ውጤት አይደርሱም ምክንያቱ ምንድን ነው?**

**መምህር ሔኖክ፡-** ማቀድ መልካም ነው ።ነገር ግን መተግበር ሊታከልበት ይገባል ።በእርግጥ ብዙዎቹ ያቀዱትን ሲተገብሩ አይታይም ።ምክንያቱ የተለያየ ሊሆን ይችላል ።ከራስ ድክመት እስከ ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ ችግሮች ያቀድነውን እንዳንተገብረው የሚያደርጉን ምክንያቶች ናቸው ።የአገር ሰላም መደፍረስም እንዲሁ ሌላው መሰረታዊ ችግር ነው ።

**አዲስ ዘመን፡- የመጪውን ዘመን ምኞትዎን ቢገልጹልን?**

**መምህር ሔኖክ ፡-** ሁሉም ብሩህ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ። ባሕረ ሐሳብን ጨምሮ አገር በቀል ዕውቀቶች ተገቢው ትኩረት አግኝተው ማየትን እመኛለሁ ።‹‹ታውቅ ዘንድ የዘመን ምሥጢር የምትመረምር አንተ ብልህ ሰው ይህን ዕወቅ፤›› የሚል ጥንታዊ ኃይለ ቃል በድርሳናት ውስጥ ይገኛልና የባሕረ ሐሳብን ልዩ ልዩ አቆጣጠሮችን እንመርምር ።ከክረምት ቀጥሎ የሚመጣው መፀው እንጂ ፀደይ አንበል ።እሱ የመጋቢት ነውና ።‹‹ቀንንና ወርን ዘመንንም ዓመትንም በጥንቃቄ ትጠብቃላችሁ›› የሚለውን መጽሐፋዊ ማስገንዘቢያንም አንዘንጋ ።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ማብራሪያ እጅግ አድርገን እናመሰግናለን።**

**መምህር ሔኖክ ፡-** ክብረት ይስጥልኝ። የከርሞ ሰው ይበለን ።

አዲስ ዘመን | እሑድ መስከረም 1 ቀን 2015 ዓ.ም



# ባህልና ቱሪዝም

# የዘመን መለወጫ ድምቀቶች- ባህልና በዓል በዕንቁጣጣሽ

**ዳግም ከበደ**

ዛሬ ወደ 2015 አዲስ አመት ተሸጋግረናል፡፡ እንኳን ከዘመን ዘመን አሸጋገራችሁ! ፀሐፊ ገጣሚና መምህር ዶክተር በድሉ ዋቅጅራ አዲስ አመትን ወይም የዘመን መለወጫን አስመልክቶ የሚከተለውን ብሏል፤ "ፍቅርና መተሳሰብን፣ ይቅርታንና መቻቻልን የነፈገንን የብሔረተኝነት ግድግዳ አፍርሰን፣ ከከረመ ደዌያችን ለመፈወስ ስንዳክር አምናን ሸኝተን፣ አዲስ ሃይማኖታዊ ከፋፋይ ግድግዳ ለማቆም ከንቸ ጠርበን ወደ አዲሱ አመት እየገባን፣ ስለምን ‹እንቁጣጣሽ!› እንባባላለን? የብሔርን ከፋፋይ አጥር፣ በብሔር የፍቅር ሰንሰለት ለመተካት፣ የዳከርንበትን አምና ፍሬ በማየት ተስፋ ሳይሆን፣ በአዲስ የሃይማኖት ከፋፋይ ግንብ ስጋት ከተቀበልነው፣ አዲስ አመት አለ? ‹እንቁጣጣሽ› መባባል አግባብ ነው? ሲል ጸሐፊው ይጠይቃል፡፡

ከልጃገረዶች ‹አበባ አየሽ ወይ - ለምለም› ቄጠማ፣ ከኮበሌዎች በቀለማት ያሸበረቀ አበባስ ስለምን እንቀበላለን! ሁሉስ ስለ አዲስ ተስፋ፣ በልባችን ስለ ሰነቅነው ብሩህ ቀን ተምሳሌት አይደለምን? ከሜዳው፣ ከሸንተረሩ፣ ከዥረቱ፣ ከአደዩና ከመስቀል ወፉ -ከተፈጥሮስ ይሁን እንጉደል፣ እንዴት ከልጆቻችን ተስፋና ምኞት እንጎድላለን? ሲልም ይጠይቃል፡፡

የዛሬውን የ2015 መስከረም አንድ የባህልና ቱሪዝም አምድ በፀሃፊ ገጣሚና መምህር ዶክተር በድሉ ዋቅጅራ ጠንከር ያለ ሃሳብ መጀመር የፈለግነው በምክንያት ነው። ኢትዮጵያ ከውስጥ በባንዳ፣ ከውጪ ደግሞ በታሪካዊ ጠላቶቿ ተከባ፣ ዜጎቿ ያለፈውን ዓመት የዘመን መለወጫ በተስፋና ስጋት ውስጥ ሆነው አሳልፈዋል። በቅርቡ የሰላም ጭላንጭል የታየ ቢመስልም ቅሉ አሸባሪው ሕወሓት በለኮሰው ጦርነት፣ የሰላም አየር እንዳይነፍስ፣ በኑሮ ውድነት እንዲፈተኑ፣ አገርና ዜጎች ሙሉ አቅማቸውን ለልማት እንዳያውሉ ተደርገዋል፡፡ በዚህ አይነቱ ወቅት ነው እንግዲህ አዲሱን 2015 አመት በዛሬው እለት የተቀበልነው።

ዘመን ተለውጧል፤ ከዘመን ጋር መለወጥ ሲገባቸው፣ መለወጥ ቀርቶ ዝግጁነቱ የሌላቸው ጥቂት አይደሉም፤ ዛሬም በአምናው መንገድ የሚሄዱ ሞልተዋል፡፡ ይህ መታረም አለበት፤ ዘመን ብቻውም መለወጡ ትርጉም የለውም፤ ዘመን መለወጡን የሚያቀነቅኑ ሁሉ፣ በዘመን መለወጥ የሚያተርፉ ሁሉ የአመለካከት ለውጥም ማምጣት ይኖርባቸዋል፡፡ ወደቀደመው አመት መመለስ እንደማይቻል ሁሉ፣ ተመልሰው መያዝ የሌለባቸው ነገሮች ወደ አዲሱ አመት እንዳይሻገሩ ለማድረግ ብዙ መስራት ይገባል፡፡

ኢትዮጵያውያን ምንም ያህል በአስከፊ ችግር ውስጥ ቢሆኑም የዘመን መለወጫን ደግ ደጉን እየተመኙ፣ ፍቅርና ሰላም እንዲመጣ ለሚያምኑት አምላክ እየተማፀኑ፣ ልጆች በወግ ባህሉ ጨዋታ ደምቀው ነው፣ ሽማግሌዎች እየመረቁ የሚቀበሉት።

ኢትዮጵያ የብሔር ብሔረሰቦች መኖሪያ፣ የታሪክ፣ የተፈጥሮና የባህል መናገሻ ነች። ህዝቦቿ በብዙ ባህላዊና ሃይማኖታዊ እሴቶች ውስጥ ሆነውና ተዋደው የሚኖሩ የፍቅርና የመከባበር ተምሳሌቶች ናቸው። አገሪቱ የራሷ የዘመን መቁጠሪያና ፊደል ያላት፤ በሌላው ዓለማት በማይገኙና ተወዳጅ በሆኑ በዓላት፣ አልባሳትና የአመጋገብ ስርዓት የምትታወቅም ነች።

ከ80 በላይ ብሔር ብሔረሰቦች መኖሪያ ብትሆንም፣ እነዚህ ብሔር ብሔረሰቦች እጅግ ብዙና ህብርን የተላበሱ እሴቶችና የጋራ ማንነቶችም ያሏቸው ናቸው። ዜጎች ከየሃይማኖታቸው ከሚቀዱ የበዓል ስርዓቶች የተገነባ ውብ ማንነት መላበሳቸው፣ በመቻቻል ለዘመናት አብሮ በመኖር ባዳበሩት እሴት የተነሳ ሁሉም የሚጋሩት ባህልና ኢትዮጵያዊ ቀለም ያላቸው መሆናቸውም እንዲሁ የማንነታቸው መገለጫ ነው።

የዘመን መለወጫ ከተበሰረበት ቀን አንስቶ "ከመስከረም እስከ መስከረም" አያሌ ተወዳጅና በጉጉት የሚጠበቁ ክብረ በዓላት፤ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ስነ ስርዓቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ይካሄዳሉ። ከዘመን መለወጫ "እንቁጣጣሽ" እስከ መስቀል፣ ኢሬቻ፣





**የባህል አልባሳት ተፈላጊነት እየጨመረ መጥቷል፤**

ጨምበላላ፣ ጥምቀት፣ ጊፋታ እና ሌሎችም በርካታ የማህበረሰቡን ባህላዊና ሃይማኖታዊ ስርዓቶች የሚያሳዩ ተወዳጅ እሴቶች በድምቀት ይከበራሉ። አገሪቱ ከውጭ ሆኖ የሚመለከታቸውን በሚያስቀኑና "የኔ በሆኑ" በሚያሰኙ ኢትዮጵያዊ ህብር ማንነቶች የደመቀችና የተወደደች ነች።

የዘመን መለወጫ ደግሞ ለምን እንደተባለና ለምን "መስከረም" ወር ላይ እንደሆነ ሊቃውንት ያትታሉ፡፡ "ብርሃናት/ፀሐይ፣ጨረቃ፣ ከዋክብት/ የዓመት ዑደታቸውን በጳጉሜን ወር ጨርሰው በመስከረም ወር ስለሚጀምሩ ነው፡፡ ያን ጊዜ ሌሊቱም ከቀኑ ጋር ይተካከላል፡፡ በሌላ በኩልም በዘመነ ኖኅ ዓለምን ውኃ አጥለቅልቋት ከቆየ በኋላ ዳግመኛ ከነበረው ውኃ የተገለጠችበት ወር «በመጀመሪያም ወር በምድር ታየች፤ የንፍር ውኃው ከምድር ደረቀ» የሚለውን መሠረት አድርገው የአቡሻኽር ሊቃውንት የዘመን መለወጫን ታሪካዊ አመጣጥ ያስረዳሉ፡፡

እንደ ሊቃውንቱ ገለፃ፤ ዘመን ተለወጠ ሲባል የሚለወጡት ወራቱ ብቻ አይደሉም፡፡ በወቅቱ የሚከሰቱት (የተከሰቱት) መልካምም ሆኑ ክፉ ነገሮች "ገጠመኝ" ሲሆኑ፣ ወራቱ ግን ያው በየዓመቱ እየተፈራረቁ ይመጣሉ፡፡

ዘመን መለወጫ ላይ የሰው ልጆች ሕይወት ሊለወጥ ይገባል፡፡ ተማሪው ተምሮ ወደቀጣዩ ክፍል (ደረጃ) የሚገባበት፣ ገበሬው የክረምትን ወራት በሚገባ ተጠቅሞ የሚቀጥሉትን የበጋ ወራት በተስፋ የሚቀበልበት፣ ሠራተኛው የክረምቱን ዝናብ ታግሶ የፀሐይን ወራት የሚቀበልበት ሌላውም እንደዚያው ሆኖ ወራቱ በዚያ ዘመን ያላቸው የተፈጥሮ ክስተቶች የሚለወጡበት ሁኔታ ዘመን ተለወጠ እየተባለ ይነገራል፡፡

**አዲስ አመት ባህላዊ ስርዓት**

**ጨለማው ሲጠፋ ዝናቡ ሲያቆም፤**

**ያ የለውጥ ወራት መጣ መስከረም።**... እያሉ ወጣት አዛውንቱ፣ ህፃናት ልጃገረዶች በተለያዩ የአገሪቱ ክፍል ያዜማሉ። ልክ እንደ ዛሬዋ ቀን (መስከረም አንድ) አዲስ ዓመት ሲመጣና "መስከረም ሲጠባ" በኢትዮጵያውያን ዘንድ ወግ ባህሉ፣ ጭፈራው ድምቀቱ እዚህም እዚያም ይታያል። በተለይ መላ ኢትዮጵያውያን በጋራ በየራሳቸው ሃይማኖታዊ ስርዓትና ባህላዊ ይዘት ይህን ቀን በድምቀት ያከብሩታል።

ከዋዜማው ጀምሮ በየቤቱ ጨፌና ቄጠማ ይጐዘጐዛል። አበባ በሥርዓት እየተዘጋጀ በየቦታው ይቀመጣል። ልጆች አዳዲስ አልባሳት ለብሰው በደስታ ይፈነድቃሉ። ቤተዘመድ ከሌላው ቀን በተለየ ይጠያየቃል። ወዳጅ ጓደኛ ስጦታ ይለዋወጣል። በዕንቁጣጣሽ መዓልት በተደመረው አድባር ሰፈርተኞች ከርቀትም ከቅርበትም ይሰበሰባሉ። አባቶች ይመርቃሉ። "ዝናቡን ዝናበ ምሕረት፣ እህሉን እህለ በረከት ያድርግልን፣ ሰላም ይስጠን፣ እህል ይታፈስ፣ ገበሬ ይረስ፣ አራሽ ገበሬውን፣ ሳቢ በሬውን ይባርክ፣ ቁንጫን፣ አንበጣን፣ ትልን... ያጥፋ፣ ምቀኛን ሸረኛን ያጥፋ፣ ወጡ ገቡ ሰቡ ረቡ የሚለውን ሁሉ እግሩን ቄጠማ ዓይኑን ጨለማ ያድርገው፣ ያርገው፣ ያረገው፣..." እያሉ ምርቃቱን ያዥጎደጉዱታል። ሁሉም ያለውን ተካፍሎ በህብረት ይበል፤ ይጠጣል። በእለቱ ጥጋብ፣ ፍቅር እና ደስታ በቀጣዮቹ ቀናት ይሆናሉ። ተስፋን ሰንቆ ፡፡

በዕለተ ዕንቁጣጣሽ በተለይ በአንዳንድ የአገሪቱ አካባቢዎች የልጃገረዶች ጭፈራና ጨዋታ እየደራና እየሞቀ ይሄዳል። በኢትዮጵያ ውስጥ በርከት ያለ ቋንቋ እና ባህላዊ ስርዓት በመኖሩ ምክንያት የዘመን መለወጫ ግጥሞችና የጭፈራ አይነቶች ሊለያዩ ቢችሉም፣ አብዛኛዎቹ ተስፋን፣ ፍቅርን፣ አብሮ መብላትን፣ የልጃገረዶችና ጉብሎች መፈላለግና መተጫጨትን እና ሌሎች የደስታ መልክቶችን የሚይዙ ናቸው። ከእነዚህ መካከል ተቀባዮቹ "ያደይ" እያሉ "ዕንቁጣጣሽ ያደይ ዕንቁጣጣሽ" "በየት ገባና ቆነጠጠሽ" "ቆነጠጠኝ ልቤን ልቤን ኩላሊቴን ፤ እናቴን ጥሩ መድኃኒቴን፤ እሙ ካልመጣች መቸም አልድን፤ እርሷን ካጣችሁ መቀነቷን፤ አበባሽ አደይ አበባዬ..." ሲሉ ያዜማሉ፡፡

**ዕንቁጣጣሽ- ባህላዊ አልባሳት**

ኢትዮጵያ ከምትታወቅባቸው በርካታ ባህላዊና ታሪካዊ እሴቶች መካከል የሕዝቦቿ ባህላዊ አልባሳት፤ ጌጣጌጥና መገልገያ ቁሳቁስ ይጠቀሳሉ። እነዚህ መድመቂያዎች ይበልጥ የሚታዩትና ተፈላጊነታቸው የሚጨምረው በዓላት በሚመጡበት ጊዜ ነው። በተለይ በዘመን መለወጫ የመስከረም ወር (በእንቁጣጣሽና በመስቀል) በዓላት ወቅት የብሔር ብሔረሰብ መገለጫ የሆኑ፣ ወቅቱን ያማከሉ ባህላዊ ዜማዎች ኢትዮጵያውያንን ያሸበርቃሉ።

ይህንን ፅሁፍ ለማሰናዳት እንዲረዳን ወደ አንድ የባህል አልባሳት ቤት ጎራ ብለን ነበር። የ"የቶቤል የአገር ባህል አልባሳት መሸጫ ሱቅ" ባለቤት አምሳል ባዬ ይህን ስራ ከጀመረች ሶስት ዓመታትን አስቆጥራለች። ወደዚህ ስራ ለመግባት ምክንያቱ "የአገሯን አልባሳት በእጅጉ መውደዷና አዘውትራ መልበሷ መሆኑን አምሳል ትገለጻለች፡፡ አልባሳቱን ለቀሪው ወገኗ በስፋት ለማስተዋወቅ፣ በውጭ አገራት ለሚገኙና በቀላሉ ምርቱን ለማግኘት ለሚቸገሩ ወገኖቿ እድሉን ለማመቻቸት ይረዳል ብላ በማሰብ ወደ ስራው መግባቷን ትናገራለች።

"በተለይ በአዲስ አመት ወይም ዘመን መለወጫ ወቅት ገበያው ይደራል፣ ትእዛዝ በብዛት እንቀበላለን" የምትለው አምሳል ባዬ፤ ኢትዮጵያውያን የአገር ባህል ልብሶቻቸውን በመስከረም ወር የዘመን መለወጫ፣ መስቀል ጥምቀትና ሌሎች መሰል ሃይማኖታዊና ባህላዊ ስነ ስርዓቶች ሲኖሩ እንደሚጠቀሙባቸው ትገልፃለች። የአደይ አበባን መፍካት፣ ልምላሜውን ለመግለፅና በብሩህ ተስፋ መሞላታቸውን ለማመልከት ቢጫ ቀለማትን የያዙ የአገር ልብሶችን እንደሚጠቀሙ ታስረዳለች።

በቶቤል የአገር ባህል ልብስ ቤት የወንድ፣ የሴት፣ የእናቶችና የወጣቶች የተለያዩ አገር ባህል አልባሳት ይገኛሉ። ቀሚስ ከነነጠላው፣ ስካርብ (የአንገት ላይ ልብሶች) ቲሸርቶች እና መሰል በርካታ ባህላዊ አልባሳት በተለያዩ ቀለማትና የጥበብ ክር ደምቀው መደርደሪያዎች ላይ ተሰቅለዋል።

አምሳል ሁሉም ሰው በሚፈልገው ዲዛይንና ቀለም አልባሳቶቹን በሸማኔዎች እንደምታዘጋጅ ተናግራ፣ እንደየጥራትና መጠናቸው ዋጋቸውም እንደሚለያይ ነው ያብራራችው። ከአራት ሺህ ብር አንስቶ እስከ ሃያ ሺ ብር ድረስ የባህል አልበሳት ለሽያጭ መቅረባቸውን ትገልጻለች፤ ከዚያም የሚያንሱና የሚበልጥ ዋጋ ያላቸው ባህላዊ አልባሳት መኖራቸውን አጫውታናለች።

**እንደ መውጫ**

የዘመን መለወጥን በማስመልከት በምሥራቅ ጎጃም ዞን በወርሃ ነሐሴና ጳጉሜ ከሚከወኑ በርካታ የማይዳሰሱ ባህላዊ ክዋኔዎች መካከል እንግጫ ነቀላ አንዱ ነው። እኛም እንደ መውጫ እንዲረዳ በልጃገረዶችና ጉብሎች በዚህ ወቅት የሚዜመውን ግጥም እንደሚከተለው አቀረብንላችሁ። ወጣት ሴቶች እንዲህ በማለት ሲያዜሙ...

«እቴ አበባዬ ነሽ
አደይ ተክለሻል
አደይ ተቀምጠሻል
ባሶና ሊበን
አዋጋው ብለሻል
ቦሶና ሊበን
ምነው ማዋጋትሽ
አንዱ አይበቃም ወይ» በዚህ ጊዜ ወንዶች ደግሞ ያዘጋጁትን ዳቦት (የችቦ ስም) በእሳት ለኩሰው እያበሩ በመምጣት እንግጫ ለሚጎነጉኑት ሴቶች ያበሩላቸዋል፡፡

ዳቦታቸውን እያበሩ ወደ ሴቶቹ በሚያመሩበት ጊዜ የሚያዜሙት አላቸው፡፡

«ኢዮሃ ኢዮሃ
የቅዱስ ዮሐንስ
የመስቀል የመስቀል
አሰፉልኝ ሱሪ
ኢዮሃ» በማለት ያዜማሉ፡፡ አዲስ ዘመንም በይፋ መምጣቱ ይበሰራል።

በመግቢያችን ላይ ለመጥቀስ እንደሞከርነው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚከናወኑ የማህበረሰቡ መገለጫ እሴቶች በሙሉ የጋራ ሃብቶች ናቸው። ከሃይማኖታዊ ፋይዳቸው በዘለለ ባህላዊ እሴቶች የሚጎላባቸው አያሌ ክብረ ባእላትም እንዲሁ ተዋደውና ተከባብረው በሚኖሩ ማህበረሰቦች መካከል ይገኛሉ። የዚህ ጥቅል ድምር ኢትዮጵያ የሚል አንድ የጋራ ማንነትን ይፈጥራል። በጥቅሉ ኢትዮጵያ ውስጥ በዓልና ባህል ልዩ መስተጋብር አላቸው። በተለይ ደግሞ "የዘመን መለወጫ" የሆነው የመስከረም ወር ሲመጣ።

ለዚያም ነው አገራችን ኢትዮጵያ የሺህ ዘመናት የአገረ መንግስት ታሪክ፣ ውብ ባህልና ማንነት ያላቸው ብሔረሰቦች በጋራ ተዋደውና በአንድነት ተጋምደው የሚኖሩባት አገር መሆኗ በገሃድ የሚታይ ሃቅ ነው ይምንለው። መልካም አዲስ ዓመት ለሁላችንም!!

# ሳምንቱን በታሪክ

# የአዲስ ዘመን ዋዜማ ገፀ በረከት

**ተገኝ ብሩ**

በኢትዮጵያ አዲስ ዘመን ተፈጥሮ በራሱ የተለየ ፍካት ይላበሳል፡፡ ሰማዩ ፈክቶ፣ ወንዙ ጠርቶ፣ ሜዳው በለምለም ሳር ተውቦ አዲስነት ይላበሳል፡፡ ተፈጥሮ እንደ አዲስ ተውቦ በሚገለጥበት በዚህ ወቅት ኢትዮጵያውያን ህይወትን በአዲስ ተስፋ ይጀምራሉ፡፡ በዛሬው «ሳምንቱን በታሪክ» ዓምዳችን አዲስ ዓመት ሲቃረብ ተወልዶ በአዲስ አመት ዋዜማ ኢትዮጵያን በዓለም አደባባይ ከፍ ያደረገን ጀግና እናስታውሳለን፡፡ ፅሁፉን ስናዘጋጅም ከተለያዩ ድረ ገፆችና ዘጋቢ ፊልሞች መረጃዎችን ወስደናል፡፡

**የአዲስ ዘመን ስጦታ**

እኤአ በ1960 የጣሊያና መዲና ሮም በኦሊምፒክ ውድድር ደምቃ ከርማለች፡፡ ኢትዮጵያ ከዚያ በፊት የኦሊምፒክ ተሳትፎ ታሪክ ቢኖራትም እስከዚያ ቀን ድረስ ምንም ሜዳሊያ ማግኘት አልተቻላትም፡፡ የውድድሩ መዝጊያ የሆነው የማራቶን ሩጫ ቀን ላይ ደርሷል፡፡ ለኢትዮጵያ ብሎም ለመላው ጥቁር ህዝብ አንድ ታላቅ ድል ሊበሰር፤ አንድ ቆፍጣና ኢትዮጵያዊ መድረኩ ላይ ይንጎማለላል፡፡

ተወዳዳሪዎች ተገርመው ያዩታል፡፡ ጥቁር ሆኖ በነጮች መሀል ቦታው ላይ መገኘቱ አልነበረም ያስገረማቸው፡፡ በእርግጥ ጥቁር ተወዳዳሪዎች በቁጥር ጥቂት ነበሩ፡፡ ነገር ግን ከዚያ በፊት ባልተለመደ ሁኔታ በባዶ እግሩ ለመሮጥ ከመካከላቸው መገኘቱ ነበር የደነቃቸው፡፡ በባዶ እግሩ ለመሮጥ መዘጋጀቱን እያዩ መሳሳቅ፤ ሁኔታውን እየተመለከቱ መገረም ውስጥ ገቡ፡፡ በዚያ የውድድር መድረክ ላይ ከዚያ በፊት መሰል ተግባር የፈፀመ ማንም አልነበረም፡፡

ይህ አትሌት ግን አገሩ አደራ ብላ የሸኘችው ታላቅ ሃላፊነትም የሚሰማው ነበርና ለእግሩ ምቹ ጫማ በማጣቱ ምክንያት ከውድድሩ ራሱን ሊያገል ፈፅሞ አልፈቀደም ፡፡ ይህ ጥቁር ቆፍጣና ሰው ቆረጠ፡፡ በጫማ መሮጥ የሚከብደውን 42 ኪሎ ሜትር በባዶ እግሩ ከባለጫማዎች ጋር እወዳደራለሁ ማለቱ ብዙዎችን አስገረመ፡፡

የውድድሩ መነሻ ሰዓት ደረሰና የጅማሮው ድምፅ ተስተጋባ፡፡ ከአንድ ሰዓት በኋላ ብዙዎች ወደ ኋላ ቀሩ፡፡ የተቀሩት መሀል ላይ ሰብሰብ ብለው ይራወጣሉ፡፡ እርሱና እጅግ በጣም በቁጥር ያነሱት ደግሞ ከፊት መምራትን ይዘዋል፡፡ በወቅቱ በመገናኛ ብዙኃን ስለ ውድድሩ ለአድማጭ ተመልካች የሚያስተላልፉት ጋዜጠኞች ከእርሱ ውጭ ያሉትን ሯጮች ደጋግመው ይጠሩና “አንድ ጥቁር” አብሯቸው አለ፤ ብቻ ነበር የሚሉት፡፡ ልጁ ግን ኢትዮጵያዊ ጀግንነትን ታጥቆ በቆፍጣና ፊቱ እየገረመማቸው ሙያ በልብ ነው ያለ ይመስል ለድሉ ራሱን አዘጋጀ፡፡

አዎ! እነርሱ የመጨረሻው ሰዓት ደርሶ እውነታውን እስኪያዩ ትኩረት አልሰጡትም ነበር፡፡ ያ በባዶ እግሩ የተመለከቱት ጥቁር ሰው፤ የጥቁር ወርቅ እንደሆነ አልገባቸውም ነበር፡፡ ለአሸናፊነት የጠበቁት ሌሎችን ነበር፡፡ ነገር ግን አበበ ቢቂላ ልበ ብርቱ ነበርና ከፊቱ የነበሩትን ከኋላ አሰልፎ የአገሩን ስም ከፍ አደረገ፤ የኢትዮጵያን ባንዲራ ሮም ላይ አነገሰ፡፡ አበበ በኢትዮጵያ ብሎም በጥቁር ህዝብ ታሪክ፤ የመጀመሪያውን የማራቶን ወርቅ አሸናፊ ሆነ፡፡ ይህ የሆነው የዛሬ 62 ዓመት በዚህ ሳምንት ነበር፡፡ የአበባ ወርቅ ትርጓሜው ብዙ ነበር፡፡ ለአገሩም ያበረከተው የአዲስ ዘመን ስጦታ፤ ልደቱንም ያከበረበት ልዩ ገጠመኝ ነበር፡፡

**“በጣም ደስ ብሎናል ምኞታችን ሞላ**
**አሸንፎ መጣ አበበ ቢቂላ ... ”**

የአትሌት አበበ ቢቂላ ልደት በዚህ ሳምንት ነሐሴ 30 ነበር፡፡ በእርግጥ አበበ ቢቂላ ለእናት ምድሩ የመጀመሪያው ድል የተቀዳጀውና የወርቅ ሜዳሊያ ያስገኘላትም ያኔ ሮም ላይ በዚሁ ወቅት ነበር፡፡

**አበበን ለኦሊምፒክ ያበቃው አጋጣሚ**

በውድድሩ ላይ ለመካፈል ወደ ጣሊያን ሊያመሩ ከተመረጡት አትሌቶች መካከል አልነበረም፡፡ በእርግጥም የአበበ እዚያ ውድድር ላይ መገኘት በአጋጣሚ ነበር፡፡ ለውድድር ሊሄዱ ከታሰቡት እና መጀመሪያ በተካሄደው ምርጫ ላይ የእርሱ ስም ፈፅሞ አልሰፈረም ነበር፡፡ ለጉዞ




አየር ማረፊያ ከተገኙት አትሌቶች መካከል አትሌት ዋሚ ቢራቱ የተባለ ሯጭ አልተገኘም፡፡

የአትሌቲክስ ቡድን አሰልጣኙ የዋሚ እግር መጎዳቱንና ለሩጫው እንደማይደርስ ተነገራቸው፡፡ ዋሚ ኳስ ሲጫወት እግሩ በመሰበሩ መሄድ እንደማይችል ያረጋገጡት ስዊዲናዊው አሰልጣኝ ኦኒ ኒስካነን፤ አበበ ቢቂላ በዋሚ ቦታ እንዲሄድና እንዲጠራላቸው አድርገው ይዘውት ሄዱ፡፡

አበበ ቢቂላ በኦሊምፒክ ታሪክ የወርቅ ሜዳሊያ ያገኘ የመጀመሪያው ጥቁር አፍሪካዊ እና በማራቶን የመጀመሪያው የወርቅ ሜዳሊያ ያገኘ ጥቁር አትሌት ነው።

**ወደ አትሌቲክስ ጉዞ**

በያኔው ስያሜ ደብረ ብርሃን አውራጃ ቦና ወረዳ ጃቶ የተባለ ቀበሌ አበበ የተወለደበት መንደር ነው፡፡ ነሐሴ 30 ቀን 1932 ዓ.ም ደግሞ ወደዚህ ምድር የተቀላቀለበት ታሪካዊ ቀን ነው፡፡ አበበ ቀድሞ ሕይወቱን የጀመረው በሩጫ አልነበረም፡፡ ልጅ እያለ እግር ኳስና ልዩ ልዩ የስፖርት አይነቶች ላይ ተሳታፊ እንደነበር በእርሱ ዙሪያ የተፃፉ ድርሳናት ያትታሉ፡፡

ወደ ሩጫው ሜዳ ያመራው በአጋጣሚ በተመለከተው ሩጫ አሸናፊዎች ሽልማት ሲበረከትላቸው በፈጠረበት መነሳሳት መሆኑን ተናግሯል፡፡ ገና በወጣትነት እድሜው በውትድርና ሙያ አገሩን ማገልገል የጀመረው አበበ የንጉስ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የክቡር ዘበኛ አባልም በመሆን አገልግሏል፡፡ የክቡር ዘበኛ ወይም በወቅቱ ወታደር የነበረው አበበ በተቀጠረበት መስሪያ ቤት የክቡር ዘበኛ ውስጥ የሩጫ ውድድር መካፈል ጀመረ፡፡ ሩጫን ዘግይቶ ቢጀምርም በስፖርቱ ትኩረትን ለመሳብ ጊዜ አልፈጀበትም፡፡

በጦር ኃይሎች ውድድር በጊዜው ታዋቂ የነበሩትን ሯጭ ዋሚ ቢራቱን አሸንፎ ከንጉሱ እጅ የወርቅ ሜዳሊያና ዋንጫ ሽልማት አገኘ። በጦር ሰራዊቱ አሰልጣኝ የነበሩት ሲዊዲናዊው አሰልጣኝ ኦኒ ኒስካነን የአበበን ችሎታ በመገንዘባቸው ከሌሎቹ አትሌቶች ጋር ተቀላቅሎ ልምምድ እንዲሰራ አደረጉ፡፡

አሰልጣኙ ትጉህና ውጤታማ አትሌቶች ለማፍራት ይጥሩ ነበርና የሮም ኦሊምፒክ እስኪቃረብ ድረስ ከ2ሺህ ሜትር በላይ ከፍታ ባላቸው ተራራማ ቦታዎች ላይ የ1500 ሜ. ተደጋጋሚ የፍጥነት ሩጫ ልምምዶችን እንዲሰሩ ያደርጓቸው ነበር።

አትሌት አበበ ለመጀመሪያ ጊዜ በማራቶን ያሸነፈው አዲስ አበባ ላይ በተደረገ ውድድር ሐምሌ ወር 1960 ዓ.ም ሲሆን ርቀቱን ለማጠናቀቅ የወሰደበት ጊዜ 2 ሰዓት ከ21 ደቂቃ ከ23 ሰከንድ ነበር።

በነሐሴ ወር ሁለተኛ ውድድሩን ሲያደርግ የመጀመሪያ ሰዓቱን ከማሻሻሉም በተጨማሪ ከዓለም በከፍታዋ ሶስተኛ በሆነችው አዲስ አበባ ከተማ ላይ ሮጦ በእንደዚህ አይነት ሰዓት ማራቶንን ከጨረሰ በሌላ ዓለም በሚደረጉ ውድድሮች ውጤታማ ሊሆን እንደሚችል አብረውት የሮጡት እና አሰልጣኞቹ ምንም ጥርጥር አልነበራቸውም።

**አበበ የነገሰባቸው የሮም ጎዳናዎች**

አበበ በአጋጣሚ ተሳታፊ የነበረበት የ1960 የሮም ኦሊምፒክ ከሌላው ኦሊምፒክ የማራቶን ውድድሮች ለየት ባለ መልኩ ነበር የተካሄደው። ማራቶኑ የሚካሄድባቸው ጎዳናዎች የከተማዋን ታላላቅና ታሪካዊ ህንጻዎች እና ቦታዎች ለዓለም እንዲታዩ ተደርገው የተዘጋጁ ነበሩ። በኦሊምፒክ ታሪክ በምሽት እንዲካሄድ የተደረገው የሮም ኦሊምፒኩ የማራቶን ውድድር በአውሮፓዊያኑ ሰዓት አቆጣጠር ማምሻውን 5:30 ላይ የማይክል አንጄሎ ንድፍ ውጤት ከሆነው ካምፒዶሊዮ አደባባይ ተጀመረ።

ውድድሩ ከተጀመረ ጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሮም ጨለመች፡፡ የመሮጫ ጎዳናዎች ግን በግራና በቀኝ ዳር ላይ በተሰለፉት የሮማ ወታደሮች ባበሩት ችቦ በሚያምር ብርሃን አሸብርቀው ነበር። የመጨረሻው የማራቶኑ ሩጫ ክፍል የሚያልፈው ደግሞ ከሺዎች አመታት በፊት የጥንታዊቷ ሮም ወታደሮች ሰልፍ እንዲያካሂዱበት ተብሎ በተገነባው ዋንኛ መንገድ ላይ ነበር።

ከውድድሩ ባሻገር ሮም ታሪኳን ለዓለም ለማሳየትና ለኦሎምፒክ እና ለማራቶን ክብር ሲባል ነበር። በዚህ ውድድር 68 የማራቶን ሯጮች ሲሆኑ ከውድድሩ አዘጋጅ ጣሊያን ጋር በታሪክ ጠላትነት ካላት የጀግኖች አባቶች እና እናቶች አገር ኢትዮጵያ የመጣው አበበ ቢቂላ አንዱ ነው።

ታላቁ ውድድር በደመቀ ሁኔታ በምሽት በዚህ ሂደት ተጀመረ፡፡ አራት አትሌቶች የብሪታኒያው ኬሊ፣ የቤልጂየሙ ቫንዴንድሪኽ፣ የሞሮኮው ረሃዲን እና አበበ ቢቂላ ከሌላው ቡድን ተነጥለው ወደፊት ወጡ።

አበበ ከሲዊዲናዊው አሰልጣኝ ኒስካነን የተነገረው የመጀመሪያ ምክር ሞሮኳዊውን አትሌት ረሃዲን “እንዳትለቅ” የሚል ነበር። አስቀድሞ 12 ማይልን ሳያልፍ በመሪነት እንደማይሮጥ የተናገረው አበበ ከረሃዲ ጋር በመሆን 16ኛው ማይል ላይ ወደፊት ከሌሎቹ ተነጥለው ወጡ፡፡

ሁለቱ አፍሪካዊያን አትሌቶች አብረው እየሮጡ እንዳለ አበበ ከፊት ለፊቱ ያየው ነገር ፍጥነቱን እንዲጨምር እና ረሃዲንን ጥሎ እንዲሮጥ አደረገ፡፡ አበበ የተመለከተው ፋሺስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ሲወር ሰርቆ ሮም ጎዳና ላይ አቁሞት የነበረውን የአክሱም ሀውልትን ነበር።

አበበ ስለ ሀውልቱ ቀድሞ አሰልጣኙ ነግሮት ነበርና ወኔ ቀሰቀሰበት፡፡ አበበ ከዚያ ሊያዝ አልቻለም። አበበ ረሃዲንን በ25 ሰከንዶች በመቅደም ርቀቱን 2 ሰዓት ከ15 ደቂቃ ከ16.2 ሰከንድ በማጠናቀቅ የዓለምን ክብረ ወሰን ሰበረ፡፡ ፈፅሞ ማንም ያልገመተውን የወርቅ ሜዳሊያ አጠለቀ፡፡ ለአገሩና ለመላው አፍሪካ ትልቅ ታሪክ ፃፈ።

**ሮምን ለብቻው የወረረ ወታደር**

ጋዜጠኞች ስለ አበበ አወሩ፤ ስለ ገድሉ ዘረዘሩ፡፡ የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎቹ የኢትዮጵያና ያዘጋጅው አገር ጣሊያን ያለፈ ታሪክ በማስታወስ “ጣሊያን ኢትዮጵያን ለመያዝ መላው ጦሯ ነበር ያሳተፈችው፤ ዛሬ ግን አበበ ቢቂላ የተባለ ኢትዮጵያዊ ወታደር ብቻውን በባዶ እግሩ ሮምን ወረረ፡፡” ብለው ዘግበውም ነበር፡፡ የኢትዮጵያ መዝሙር ጣሊያን ላይ በክብር መዘመሩም ትልቅ ድል ነበር፡፡

**አበበ ዳግም በኦሊምፒክ ድል**

በባዶ እግሩ ሮም ላይ ሮጦ በማራቶን ዓለምን መቆጣጠሩ ሳያንስ እ.አ.አ በ1964 ቶኪዮ ኦሊምፒክ ላይ በማራቶን ውድድር በጫማው ሮጦ የወርቅ ሜዳሊያን አስገኘ፡፡ ነገር ግን ይህ ብቻ አልነበረም አስገራሚው ነገር፡፡ የኦሊምፒክ ውድድሩ ከመጀመሩ 40 ቀናት ቀደም ብሎ የትርፍ አንጀት ሕመም ገጥሞት ሆስፒታል ገብቶ የቀዶ ጥገና ተደርጎለት በደንብ ሳያገግም ማሸነፉ ነበር አጀብ ያስባለ ገድሉ፡፡

78 ሯጮች በተሳተፉበት በቶኪዮው ኦሊምፒክ የማራቶን ውድድር ላይ አንደኛ በመውጣት ውድድሩ ለመመልከት የታደመው 70 ሺህ ተመልካች ማመን በማይችልበት ሁኔታ ርቀቱን 2 ሰዓት ከ12 ደቂቃ ከ11.2 ሰከንድ በሆነ ጊዜ አጠናቆ የዓለምን ክብረወሰን በመስበር በሁለት ተከታታይ ኦሊምፒኮች በማራቶን አከታትሎ ሁለት የወርቅ ሜዳሊያዎችን ያገኘ ብቸኛ አትሌት ለመሆን በቅቷል።

**አሳዛኙ መጨረሻ**

መጋቢት 15 ቀን 1961 ዓ.ም የተሰማው ዜና፤ ኢትዮጵያዊያንን ብቻ ሳይሆን መላውን የስፖርት አፍቃሪ ቤተሰብ ያሳዘነ ነበር። አበበ ከአዲስ አበባ 70 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ከባድ የመኪና አደጋ ደረሰበት። ለህክምና ወደ እንግሊዝ ተልኮ ለስምንት ወራት ያህል ሲታከም ቢቆይም እነዚያ ተአምር የሰሩ እግሮቹ ሊራመዱለት አልቻሉም፡፡ ታላቁ አትሌት ከወገቡ በታች አካል ጉዳተኛ ሆነ። ነገር ግን አትሌቱ ብርቱ ነበርና በሌሎች የውድድር ዘርፎች መሳተፉን ቀጠለ፡፡

አበበ እንግሊዝ አገር በተካሄደ የቀስት ውድድር አሸንፏል፡፡ ኖርዌ ላይ በተካሄደ የዊልቸር የ25ኪ.ሜ የአገር አቋራጭ ውድድር እንዲሁም ከሶስት ቀናት ቆይታ በኋላ በተካሄደው የ12 ኪ.ሜ ውድድር አንደኛ በመውጣት የወርቅ ሜዳሊያ ተሸልሟል፡፡ ታላቁ አትሌት አበበ ቢቂላ በጥቅምት ወር 1973 ዓ.ም በ41 አመቱ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ፡፡ ተዓምረኛው ጀግና አትሌት አበበ ቢቂላ፤ የሰራቸው ገድሎች በወርቃማ ፅሁፍ ተከትቦ ዛሬ ድረስ ይወሳል፡፡

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

## ባለ ዋሽንቱ - አቡ ገብሬ ኬቶ

**አቤል ገብረኪዳን**

10ኛው የበጎ ሰው ሽልማት ባለፈው እሁድ ነሐሴ 29 ቀን 2014 ዓ.ም ተካሂዷል ። በ9 የተለያዩ ዘርፎችም በህዝብ ጥቆማ ከተሰጠባቸው ከ700 በላይ በጎዎች መካከል 27 እጩዎች ቀርበው ተሸልመዋል ። ከዘጠኙ ዘርፎች መካከል አንደኛው የቅርስና ባህል ዘርፍ ሲሆን የመጨረሻዎቹ እጩዎችም አቶ አቡ ገብሬ ፤ ሐጂ መሀመድ አወል ሀምዛ እና መምህር ዜና ማርቆስ እንዳለው ሆነዋል ። በዛሬው እትማችን ባለዋሽንቱን በጎ ሰው አቡ ገብሬን የሕይወት ታሪክ በመርሀ ግብሩ ላይ ከቀረበው ግለ ታሪኩ በመውሰድ እንቃኛለን ።

አቡ ገብሬ ኬቶ በ1966 ዓ.ም አዲስ አበባ፤ ሽሮሜዳ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ተወለደ ። እድሜው ለትምህርት ሲበቃ በ1975 ዓም አምሃ ደስታ ትምህርት ቤት በመግባት ከ1ኛ እስከ 8ኛ ክፍል የተከታተለ ሲሆን የ8ኛ ክፍልን በጥሩ ውጤት አልፏል ። አቡ ገብሬ በ1983 ዓ.ም የ9ኛ ክፍል ተማሪ በነበረበት ወቅት የሙዚቃ ዝንባሌ ስለነበረው ዝንባሌውን ከትምህርት ጎን ለጎን ያስኬድ ነበር ። በወቅቱም ከአማተር ቴአትር ክበባት ጋር በመሆን ሙዚቃ መሳሪያ በመጫወትና በማዜም ያሳልፍ ነበር ።

በ1986 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና በወሰደበት ዓመትም በህጻናትና ወጣቶች ቴአትር ለመቀጠር በቃ ። አቡ ይሄን አጋጣሚ ለቀጣይ ሕይወቱ መስፈንጠሪያና ለዛሬው ማንነቱ መሰረት የጣለበት አጋጣሚም ሆነ ። በህጻናትና ወጣቶች ቴአትር ቤት ተቀጥሮ የተለያዩ ባህላዊና ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች የማግኘት እድል ስለነበረው የጊታር፣ የዋሽንት፣ የክራር ችሎታውን ለማዳበር ችሏል። ይሁን እንጂ የዋሽንት ዝንባሌው እያየለ በመምጣቱ በዚሁ ዘርፍ ብዙ ስራዎችን ለመስራት በቅቷል ።


አቡ የተለያዩ ቦታዎች በመዘዋወር ሙዚቃን በመጫወት የግልም የቡድንም ልምድ አካብቷል። በስራ ውስጥ በሚገኝና በሚፈጠር ውይይትና መተጋገዝ ራሱንም ሆነ የቡድን ጓደኞቹን በእውቀትና ልምድ ደግፏል ። በተለያዩ ታዋቂ ሆቴሎች ለ18 ዓመታት ከመደበኛ ስራው በኋላ የባህል ምሽቶችን በመዘዋወር ተጫውቷል ።

በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ የአገራችን ባህላዊ ዘፈኖች ላይ በመሳተፍ ትልቅ እውቅናን ያተረፈ ሲሆን ኤፍሬም ታምሩ እና ጎሳዬ ተስፋዬ በጋራ ያዜሙት ‹‹ኑኑ››፣ ታደለ ሮባ የተጫወተው ‹‹ኢትዮጵያ››፣ የዳዊት ጽጌ አልበም ‹‹የኔ ዜማ››፣ የጃኖ ባንዱ ሀሌሉያ ተክለጻዲቅ የተጫወተችው ‹‹ሸግዬ››፣ የኛ የሙዚቃ ቡድን የተጫወቱት ‹‹አቤት››፣ የሚካኤል በላይነህ ‹‹ስቁ ሸኝሻለሁ››፣ የራሄድ ጌቱ ‹‹ኢትዮጵያ››፣ የወንዴ ማክ ‹‹በውይይት›› እና ሌሎችም ላይ ተሳትፏል ። ከአስቴር አወቀ፣ ጸደንያ ገብረማርቆስ፣ አበባ ደሳለኝ እና ሌሎች ታዋቂ ድምጻውያንም ጋር እንዲሁ አብሮ ሰርቷል ።

አቡ ለሙዚቃው ኢንደስትሪ ካበረከታቸው ስራዎች ውስጥ አንዱ በርካታ ወጣቶች ክራር ተጫዋች እንዲሆኑ ሙያውን ማጋራቱ ነው ። ዛሬ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ የሚገኙ ስመጥር ወጣት የክራር ተጫዋቾች የአቡ ሙያዊ እገዛ የተቸራቸው ናቸው ። በተለይም የኢትዮጵያ የባህል መሳሪያ በሆነው ዋሽንት ዙሪያ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተማሪዎችና ተመራማሪዎች ጥናት ሲያካሂዱ ለምርምር የራሱን አበርክቶ ሰጥቷል ። ሁለት የውጭ አገር የሙዚቃ ምሁራንም ዋሽንትን ለማጥናት በመጡበት ወቅት የሙያ ተሞክሮውን አካፍሏል ።

አቡ ገብሬ የኢትዮጵያ ሙዚቃ በተለያዩ የውጭ አገራት በተዘጋጁ የሙዚቃ ኮንሰርቶች ላይ በመሳተፍ ስራውን አቅርቧል ። ጀርመን፣ ሰዊዘርላንድ፣ እስራኤል፣ ቻይና፣ ጃፓን፣ ዴንማርክ፣ ፈረንሳይ ወዘተ በተደጋጋሚ ተዘዋውሮ የሰራባቸውና የኢትዮጵያን ባህላዊ ሙዚቃ ያስተዋወቀባቸው አገራት ናቸው ።

ከአስር ዓመታት ወዲህ ደግሞ የአቡ ዋሽንት ያልገባበት ቦታ የለም ማለት ማጋነን አይሆንም ። ከ100 በላይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ዶግማ፣ ቀኖናና እና ትውፊት የተሰሩ መዝሙሮች ላይም ተሳትፏል ። በሲኒማው ኢንደስትሪም የአቡ



አበርክቶ ከፍተኛ ነው ። ጤዛ፣ አልቦ፣ አትሌቱ እና ዓባይ ወይስ ቬጋስ በዋሽንት ከተሳተፈባቸው ስራዎች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው ። አቡ ሰርከስ ኢትዮጵያ መስራች አባልም ነበር ። ዋሽንቱን ይዞ ሰርከስ ኢትዮጵያን ካቋቋሙት ሰዎች መሀከል አንዱ ሆኖ ተሳትፏል ። በባላገሩ አይዶል ላይ የመክፈቻ ፕሮግራሙን እንዲሁም ከአንድ እስከ ሶስተኛ ዙር ያለውን ውድድር አጅቧል ። አቡ በአሁኑ ጊዜ በሀገር ፍቅር ቴአትር እየሰራ የሚገኝ ሙዚቀኛ ነው ።

## ሱፐር ሞዴል አና ጌታሁን

ሱፐር ሞዴል አና ጌታነህ መሰረቷን አሜሪካና ፈረንሳይ አድርጋ በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ የሆነችበትን የሞዴሊንግ ስራን ለበጎ አድራጎት ያዋለች የአገር ልጅ ናት ። አና የተወለደችው በስዊድን ሲሆን በአባቷ ዲፕሎማትነት ምክንያት አብዛኛው እድገቷ በውጭ አገራት ቢሆንም የኢትዮጵያ አገሯን ቋንቋዋንና ባህሏን እያስተማሩ አሳድገዋት ከወላጆቿ ጋር በተለያዩ አገራት በመዘዋወር የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ተከታትላለች ። በቤልጀየም በማርኬቲንግ የትምህርት ዘርፍ የዩኒቨርሲቲ ትምህርቷን ተከታትላም ተመርቃለች ። የስዊድን ቋንቋ አፍ መፍቻዋ ቢሆንም አማርኛ ፈረንሳይኛ እና እንግሊዝኛን አቀላጥፋ ትናገራለች ።

አና በፈረንሳይ እና አሜሪካ የሞዴሊንግ ጥበብን ተምራለች፤ ሰርታለችም ። በመቀጠልም ወደ ደቡብ አፍሪካ ተዛውራ ለ10 ዓመት በሞዴሊንግ ስራ በርካታ ተግባራትን ፈጽማለች ። በዚህ ወቅት አፍሪካን ሞዛይክ የተሰኘውን ተቋም መስርታ በርካታ አፍሪካውያን በአንድነት የአፍሪካን የፋሽን ጥበብ ለዓለም እንዲያሳዩ አድርጋለች ። እንደ ውጭ አገሩ ሁሉ ይህን የፋሽን ትርኢት በኢትዮጵያም አካሂዳለች ። የአና አፍሪካን ሞዛይክ በአሜሪካን በግብረ ሰናይ ድርጅትነት የተመዘገበ ነው። በሞዴሊንግ ሙያ ያገኘችውን ዓለም አቀፍ እውቅናና ሀብት ኢትዮጵያውያንን ለመርዳት አውላዋለች ።

ገና በልጅነቷ ፍርቱናዋን ያወቀችው እና በዚህም የተሳካላት አና ሞዴሊንግ አንድ ወጥ የሆነ ፎርሙላ የለውም ትላለች ። ሞዴሎችም ራሳቸውን ከሌላው ጋር ማወዳደር እንደሌለባቸው ትናገራለች ። ስለዚህም ሞዴሊንግ ውስጥ የሚሳተፉ ሰዎች በተለይም ሴቶች እድሉን ካገኙ መጠቀም እንዳለባቸው ነገር ግን ብቸኛ ተስፋዬ እሱ ነው ብለው



መቀመጥ እንደሌለባቸው ትመክራለች ። ብዙ ሰዎች ‹‹ፊቴን መቀየር አለብኝ፣ በጣም መክሳት አለብኝ፣ ምግብ አበላሌን መቀየር አለብኝ፣...›› በማለት በመልካችን ላይ ብቻ መጠመድ ሌላ አይነት ችግር ሊፈጥር ይችላልም ትላለች ።

አና ከውጫዊ ገጽታዋ በላይ በውስጣዊ ማንነቷ ላይ አትኩራ እንደምትሰራ ትናገራለች ። ለሃይማኖቷ ትኩረት እንደምትሰጥ እንዲሁም ለስኬቷ ባለቤቷ አቶ አድማሱ እንደሚያግዛት ትናገራለች ። ለቤተሰብ ጊዜ መስጠት፣ ከመጠን በላይ ራስ ላይ ጫና አለመፍጠር እና ነገሮችን ተረጋግቶ ማስኬድ ከህይወቷ ያገኘችው ተሞክሮ ነው ። የእናቷ ከፍተኛ የሆነ በጎ ተጽእኖ እንዳለባት የምታነሳው አና እናቷ ጀግናዋ እንደሆኑ ትናገራለች። በሞዴሊንግ ዙሪያ አባቷ እና እናቷ የተለያየ አቋም ነበራቸው ። አባቷ የምዕራቡን ዓለም የሚያውቁ ዲፕሎማት ቢሆኑም እንደ ብዙው ኢትዮጵያዊ አባት ቆጠብ ያሉ ሰው ናቸው ። በዚህም የተነሳ የልጃቸውን የሙያ ምርጫ በቀላሉ አልተቀበሉትም ። እናቷ በበኩላቸው ዲዛይነር በመሆናቸው የልጃቸውን ምርጫ ለመቀበል አልከበዳቸውም ። በዚህም የተነሳ እናትና አባት በዚህ ዙሪያ ለመስማማት ጊዜ የወሰደባቸው ሲሆን በኋላ ግን አባት የሚስትን ሀሳብ ተቀብለው ልጃቸውን መደገፍ ጀምረዋል ። በወቅቱ በነበሩት ጥቂት እድሎችም ተጠቅማ ከነበሩት ጥቂት ጥቁር ሞዴሎች መካከል አንዷ ሆና በስኬት መጓዝ ችላለች ።

ገና በልጅነቴ በቂ ገንዘብ አግኝቻለሁ ስኬታማም ነበርኩ የምትለው አና በወቅቱ የነፍሴ ጥሪ ምን እንደሆነ ራሴን እጠይቅ ነበር በማለት ልቧ ገና ያኔ ተመልሳ አገሯ መኖር እና ህዝቧን ማገዝ ትመኝ እንደነበር ትናገራለች ። ተመኝታም አልቀረች ሁኔታዎች ሲመቻቹላት ወደ አገሯ ለመመለስ እና ህዝቧን ለማገዝ አላመነታችም ።

በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን አለልቱ ከተማ ከ22 ዓመት በፊት በመሰረተችው ትምህርት ቤት ለበርካታ ኢትዮጵያውያን የእውቀት ብርሃንን አብርታለች ። አና ትኩረቷን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ለአካባቢው ወጣቶች በነጻ ማዳረስ መሆኑን ትናገራለች ። በአለልቱ ከተማ በከፈተችው ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች ትምህርታቸውን በነጻ ያገኛሉ፤ ምግብ በቀን ሶስት ጊዜ ይመገባሉ ። ወደ መኖሪያቸው ሲመለሱም ምግብ በቤታቸው ለማግኘት የሚቸገሩ ከሆነ ይዘው የመሄድ መብት አላቸው ።ተማሪዎቹ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሻገሩም ድጋፉ አይለያቸውም ።

አና ከ25 ዓመታት በፊት ያቋቋመችው የኢትዮጵያ ህጻናት ፈንድ የተሰኘው የበጎ አድራጎት ተቋም ከላይ በተገለጸው ትምህርት ቤት ከ800 በላይ ተማሪዎችን ያስተምራል ። ከዚህ ትምህርት ቤት ተነስተው የዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን አጠናቅቀው ራሳቸውን የቻሉ አያሌ ኢትዮጵያውያን አሉ ። የአካባቢው ማህበረሰብ በምጣኔ ሀብት ራሱን የሚችልበት በርካታ የራስ አገዝ ስራዎችን ያከናውናል። ከዚህ ባለፈ በሙያዋ አዳዲስ ዲዛይነሮችን ለመፍጠር የግሏን ጥረት እያደረገች ሲሆን አንደኛው በጎ ተጽእኖዋ ይህ እንዲሆን እንደምትፈልግ ትናገራለች ። ጥጡም ቆዳውም ሌላውም እኛ ጋር አለ ስለዚህ እኛ ሌሎችን ለመምሰል ከመሞከር ይልቅ የራሳችን አዲስ መንገድ መፈለግ አለብን ስትልም ለዲዛይነሮች ትመክራለች ።

አና በበጎ ስራዋ በዘንድሮው የ10ኛው የበጎ ሰው ሽልማት በጎ ባደረጉ ዲያስፖራ ኢትዮጵያውያን ዘርፍ ከሶስት የመጨረሻ ተሸላሚዎች አንዷ ሆናለች። ባለፈው ዓመትም የጣሊያን መንግስት እና የኢትዮጵያ እና የጣሊያንን ወዳጅነት ለማጠናከር ባደረገችው ተግባር የኢጣሊያ ከፍተኛው ሽልማት የሆነውን ኦፊሰር ኦፍ ኦርደር ኦፍ ዘ ስታር ከአገሪቱ ፕሬዚዳንት ተበርክቶላታል ።

# ዓለም አቀፍ

## ንጉሥ ቻርለስ ሦስተኛ በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ ለማገልገል ቃል ገብተዋል



የእናታቸውን ሞት ተከትሎ የንግሥና መንበሩን የተረከቡ ንጉሥ ቻርለስ በመጀመሪያው ንግግራቸው “በአግባቡ የተኖረ ሕይወት” ሲሉ “ተወዳጇን እናታቸውን” አሞካሽተው በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ ለማገልገል ቃል ገብተዋል። ስሜታዊነት በተቀላቀለበት የመጀመሪያ ንግግራቸው ንጉሡ፣ የንግሥት ኤልዛቤጥ እንክብካቤን፣ ቀልድን እና በሰዎች ውስጥ ያሉ መልካም ነገሮችን የመመልከት ብቃታቸውን አድንቀዋል።

ንጉሥ ቻርለስ ሦስተኛ፣ ዊሊያም እና ካትሪን የዌልስ ልዑልና ልዕልት እንደሚሆኑ ተናግረው፣ ለልዑል ሄሪ እና ለባለቤቱ ሜጋን ያላቸውን ፍቅር ገልጸዋል።ንግሥት ኤልዛቤጥ ሐሙስ ዕለት ስኮትላንድ ባልሞር ውስጥ ነበር ያረፉት። የንጉሡ ንግግር የተላለፈውም ቅዱስ ጳውሎስ ካቴድራል ውስጥ ለንግሥቲቱ የተሰናዳው መታሰቢያ በሚካሄድበት ወቅት ነበር።

የ73 ዓመቱ ንጉሥ በንግግራቸው የንግሥቲቱ “በተለያዩ ለውጦች ውስጥ፣ በደስታ እና በመልካም ጊዜ፣ እንዲሁም በመጎዳት እና በሐዘን ወቅት ሁሉ፤ ለኃላፊነታቸው የማይናወጥ መሰጠት ነበራቸው” ብለዋል።ንጉሡ፣ ልጃቸው የሆነውን ዊሊያም የዌልስ ልዑል ባለቤቱን ካትሪንን ደግሞ የዌልስ ልዕልት አድርገው መሰየማቸውን ይፋ አድርገዋል።

ጨምረውም “በባሕር ማዶ ሕይወታቸውን መምራት ለመረጡት ለሄሪ እና ሜጋን” ያላቸውን ፍቅር ገልጸዋል።ንግሥት ስለሆኑት ለ17 ዓመታት በትዳር ስለተጣመሯቸው የ75 ዓመቷ ካሚላም “ለሚጠበቅባት አዲስ ኃላፊነት በጽኑ እንደምትቆም እና ለእኔም ድጋፍ እንደምትሆነኝ አውቃለሁ” ብለዋል። ንጉሡ ኃላፊነታቸውን ከተረከቡ በኋላ ሕይወታቸው መለወጡንም አመልክተዋል።

“ለበጎ አድራጎትና ለሌሎች ጉዳዮች ከዚህ በፊት ሳደርገው እንደነበረው አብዛኛውን ጊዜዬን እና ጉልበቴን መስጠቴ ያበቃል፤ ነገር ግን እነዚህ አስፈላጊ ተግባራት በሌሎች አስተማማኝ ሰዎች እንደሚከወኑ አውቃለሁ” ብለዋል ንጉስ ቻርለስ። የዙፋናቸው አልጋ ወራሽ ልዑል ዊሊያም፣ የንጉሥ ቻርለስ የቀድሞ የስኮትላንድ ማዕረግ እና ኃላፊነት የሆነውን የኮርንዌል አልጋ ወራሽነትን ይረከባሉ።

“አዲሱ የዌልስ ልዑል ካትሪንን ከጎኑ አድርጎ፣ የሚጠበቅበትን ኃላፊነቶች ሁሉ ያከናውናል። የሚያስፈልገው ድጋፍ ሁሉ ይደረግለታል” ብለዋል ንጉሡ። ስለእናታቸውም “ለቤተሰባችን ለነበረሽ ፍቅር እና ላደረግሽው ነገር ሁሉ እንዲሁም ለዘመናት በትጋት ላገለገልሻቸው ሕዝቦች አመሰግንሻለሁ” ብለዋል።

ንጉሥ ቻርለስ የንግሥና መንበሩን እንደተረከቡ ቀዳሚ ኃላፊነታቸው የሆነው ከጠቅላይ ሚኒስትር ሊዝ ትረስ ጋር ባኪንግሃም ቤተ መንግሥት ውስጥ ተገናኝተው ተወያይተዋል። ዓርብ ዕለት በዌስት ሚኒስቴር ውስጥ በተካሄደው ንግሥቲቱን የማሰብ የጸሎት ሥነ ሥርዓት ላይ የፓርላማ አባላት እና ባለሥልጣናት ተገኝተው ነበር።

ጠቅላይ ሚኒስትር ትረስ ንግሥቲቱን “ዓለማችን እስካሁን ካየቻቸው ታላላቅ መሪዎች አንዷ ነበሩ” ብለዋቸዋል። የንጉሡ ቤተ መንግሥት በቀጣይ ቀናት ስለሚከናወኑ ነገሮች ዝርዝር ጉዳዮችን ይፋ አድርጓል። እስካሁን የንግሥቲቱ የቀብር ሥነ ሥርዓት መቼ እንደሚፈጸም የተቆረጠ ቀን ባይኖርም በቀጣዮቹ ሁለት ሳምንታት ውስጥ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል።

ከቀብር ሥነ ሥርዓቱ በፊት የንግሥቲቱ አስከሬን ኤደንብራ ውስጥ ከቆየ በኋላ ወደ ለንደን ይወሰዳል። ለንደን ውስጥ በሚገኘው የዌስት ሚኒስቴር አዳራሽ አስከሬኑ ለሕዝብ ክፍት ተደርጎ በአጠገቡ እያለፉ አክብሮታቸውን በመግለጽ እንዲሰናበቱ ይደረጋል።

---

### የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ

ንብረትነቱ አቶ ስላሴ ሲርኮ የሆነ የሠሌዳ ቁጥር ኮድ 1-25584 ደ/ህ የሞተር ቁጥር የሞተር ቁጥር AK4BL4004243 የሻንሲ ቁጥር EAYACARWALG020041 የሆነ ባለሶስት እግር ተሽከርካሪ ሰሌዳው /ታርጋ/ ጠፍቶብናል በማለት በቀን 27/12/2014 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡
ስለዚህ ሠሌዳውን ወድቆ ወይም ተሰርቆ ሌላ ሰው ሲጠቀም ያገኘ ሰው ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሰባት ቀን ውስጥ ሪፖርት እንዲያደርግ እየጠየቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረበ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**የጋሞ ዞን ትራንስፖርትና መንገድ ልማት መምሪያ**

### ኦሮሚያ ክልል

የባለንብረቱ ስም የወ/ሮ መሰረት ጌታቸው አበበ የሰሌዳ ቁጥር 1-10722ኦሮ ሊብሬ ቁጥር G0005195 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በቀን 13/10/14ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ በዚሁ መሰረት የተሽከርካሪውን ሊብሬ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ሊብሬ በምትክ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**የሰሜን ሸዋ ዞን ትራንስፖርት ባለሥልጣን**

### ድሬዳዋ አስተዳደር

ከሳሽ አቶ ስሜነህ መንግስቱ እና በተከሳሾች እነ አቶ ተስፋዬ አሻግሬ (5) ሰዎች መካከል ስላለው የፍትሐብሔር ክስ ክርክር ጉዳይ ተከሳሾች በአድራሻቸው የታጡ በመሆኑ ተከሳሾች የከሳሽን ክስ ከሬጅስትራር ቀርበው በመውሰድ የፅሁፍ መልሳቸውን ለ4/01/2015 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት በሬጅስትራር በኩል እንዲያቀርቡ እና ክሱ በ11/01/2015 ዓ.ም ሊሰማ የተቀጠረ መሆኑን አውቀው በእለቱ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ቀርበው እንዲከራከር ይህ ባይሆን ግን ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ተከሳሾች በሌሉበት በማየት ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን የድ/ዳ/አስ/መ/ደ/ፍ/ቤት ድሬዳዋ ምድብ 3ኛ ፍታብሔር ችሎት አዟል፡፡

**የድሬዳዋ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

የባለንብረቱ ስም አቶ አህመድ ጃቢር ሰሌዳ ቁጥር 03-06566 ድሬ የተሽከርካሪ ዓይነት የጭነት የሻንሲው ቁጥር፡JAAKP34H7M7P03749 ሞዴል WPPRP711የሞተር ቁጥር ፡4HG1-UFR114 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ 20/17/2013 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ሰሌዳው ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**የድሬዳዋ አስተዳደር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ባለሥልጣን**

### አማራ ክልል

የባለንብረት ስም አቶ ዳንኤል የሻበል የተሽከርካሪው ሰሌዳ ቁጥር አማ-01-02291 የተሽከርካሪው አይነት አውቶቡስ ሞዴል KCLH113V-SPRMS የተሽከርካሪው የአገልግሎት አይነት ለከተማ ታክሲ አይነት የሞተር ቁጥር 3L-4360258 የቻንሲ ቁጥር LH113-0159525 የተሽከርካሪው የመጫን አቅም 10 ሰው የአመታዊ ምርመራ ቀን 19/12/2013ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ሠሌዳ ወድቆ፣ ተሠርቆና በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ህጋዊ ማስረጃ ይዞ ይቅረብ፡፡ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**ባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ጽ/ቤት**

ንብረትነቱ ፉአድ ሰይድ የሆነ አውቶብስ ተሽከርካሪ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 1-19762 አማ ሰሌዳ የጠፋ መሆኑን ባለንብረቱ በ12/12/2014 ዓ.ም በተፃፈ አመልክቷል፡፡ ሰሌዳው ወድቆ ተሰርቆ ወይም በሌላ ግለሰብ እጅ ላይ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ሪፖርት እንዲያደርግ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑ እንገልፃለን፡፡

**በሰ.ብ.ክ.መ ትራንስፖርት ሎጀስቲክ ባለሥልጣን ደቡብ ወሎ ዞን ትራንስፖርት ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ማለደ መንግስቱ የሰሌዳ ቁጥር 26462 የተሽከርካሪ ዓይነት ባጃጅ የሻንሲ ቁጥር 37262 የተሽከርካሪ ሞዴል RE 45 የሞተር ቁጥር 82374 የሊብሬ ቁጥር 064295 ከላይ የተጠቀሰው ባለንበረት የተሽከርካሪው ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ17/12/2014 ዓ.ም. አመልክተዋል፡፡ ስለሆነም ሰሌዳውን ወድቆ፣ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ የማ/ጎንደር ዞን መንገድና ትራንስፖርት መምሪያ**

### አዲስ አበባ አስተዳደር

በከሣሽ ወ/ሮ ሀገሪቱ እንድሪስ ሙሄ እና በተከሣሽ አቶ አህመድ ሙሀመድ መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ መከሰስዎን አውቀው መስከረም 09 ቀን 2015 ዓ.ም በ8፡00 ሰዓት የተቀጠረ መሆኑን አውቀው አ/አ/ከ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የቦሌ ምድብ ችሎት**

የባለንብረት ስም ስዩም ካሴ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-A09085 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር ZZ5BLSF7MN764763 ሞዴል ZZ1257S4341W የሞተር ቁጥር WD615.47*210107022997* የሊብሬ ቁጥር 0239511 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ26/12/2014 ዓ.ም. አመልክተዋል፡፡
ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የየካ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ናትናኤል ሙሉጌታ ደምሴ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-A20407 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ11 ኩንታል ያነሰ የሻንሲ ቁጥር MMBCNKB407D069709 ሞዴል L200 የሞተር ቁጥር 4D56- DCAL0646 የሊብሬ ቁጥር 198346/312646/308508 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ9/12/2014 ዓ.ም. አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቦሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ሐጅ ከበደ ሠይድ አማን/የሞቴል በለ ኮኮብ/3ኮከብ/ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-92331 የተሽከርካሪው አይነት ድርብ አገልግሎት የሻንሲ ቁጥር ROFR22G8DO628711 ሞዴል KUN25L-PRMDHV የሞተር ቁጥር 2KD-5974454 የሊብሬ ቁጥር 181163 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ26/12/2014 ዓ.ም. አመልክተዋል፡፡
ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የየካ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**


የባለንብረት ስም ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሰሌዳ ቁጥር ኢት 04-01-18631 የተሽከርካሪው አይነት ድርብ አገልግሎት የሻንሲ ቁጥር JN1CJUD22Z0079513 ሞዴል CVRULCFD22NWNY562Z የሞተር ቁጥር QD32225247 የሊብሬ ቁጥር 0080601 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ24/12/2014 ዓ.ም. አመልክተዋል፡፡
ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቂርቆስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**




# አዲስ ዓመትና ልጆች

**ጽጌረዳ ጫንያለው**



ሰላም ልጆች እንዴት ናችሁ፤ ዛሬ እንኳን አደረሳችሁ ብዬ ልጀምር አይደል? ምክንያቱም አዲስ ዓመት ላይ ስንሆን ዋና ሰላምታችን ይህ ነው ።ክረምቱ አልፎ ሰማዩ የሚጠራበትን እለት አምላካችን ስለሰጠን የምናመሰግንበት ጊዜም ነውና እንኳን አደረሳችሁ መባባል አለብን ።ለመሆኑ ይህንን በዓል እንዴት ለማሳለፍ አስባችኋል፤ መጪውን የትምህርት ዘመንስ በምን መልኩ ለማሳለፍ አቅዳችኋል? እርግጠኛ ነኝ ብዙዎቻችሁ ዝግጅታችሁን ጨርሳችሁ የመግቢያ ቀናችሁን እየጠበቃችሁ ነው ።ምክንያቱም ይህ ጊዜ የናፈቋችሁን የትምህርት ቤት ጓደኞቻችሁን የምታገኙበት ነው ።በዚያ ላይ ከትምህርት ተለይታችሁ ቆይታችኋልና ያንን የናፈቃችሁትን ትምህርት መማር የምትጀምሩበትም ነው ።

በዚህ ወቅት ዘመዶቻችሁን ጭምር የምትጠይቁበትም ሊሆን ይችላል ።ምክንያቱም ክረምቱ አልፎ መስከረም ይጠባልና ነው ።በዚያ ላይ ሜዳው በሙሉ በአበባ የሚያሸበርቅበት ጊዜ ስለሆነ እንደልባችሁ ለመቦረቅና ከጓደኞቻችሁ ጋር ለመጫወት የምትችሉበት ወቅትም ነው ።እናም ይህ አዲስ ዓመት ሲመጣ ብዙዎቻችሁ እንደተደሰታችሁ ይሰማኛል ።ለመሆኑ ልጆች አዲስ ዓመት፤ እንቁጣጣሽ፤ ቅዱስ ዮሐንስና አውደ ዓመት የሚባለው ለምን እንደሆነ ታውቃላችሁ ? ለዛሬ ስለዚህ ነገር ትንሽ ልበላችሁ ።

አዲስ ዓመት ለምን ተባለ ከተባለ መልሱ ይህ ነው። በሰኔ ወር የገባው የክረምት ወቅት እየበረታ ሰማዩ በመብረቅ ብልጭታና በነጐድጓድ ድምፅ የሚታጀብበት፤ ከላይ የዝናብ ዶፍ ከሥር ጐርፍ የሚጨምርበት፤ አልፎ ተርፎም በረዶ የሚዘንብበት ጊዜ ነው። መስከረም ሲሆን ግን ሁሉ ነገር ይለወጣል ።ምድሪቱ በልምላሜ ትሞላለች ።አስፈሪዎቹ ከሰኔ እስከ ነሐሴ ያሉ ወራት ይለወጡና ምድሪቱን በበረከት ይሞሏታል ።በምድር ላይ አዲስ የሆኑ ነገሮች በስፋት ይታያሉ ።አንዱ ፀሐይ መውጣቷ ሲሆን፤ የበረደው ይሞቀዋል፣ የጨለመውም ብሩ ይሆናል፤ የረጠበውም ይደርቃል ።በክረምቱ ዝናብ ረግፈው የነበሩት አበባዎች ሳይቀሩ ዳግመኛ ሕይወት ያገኛሉ። ንቦች በየጋራው በየሸንተረሩ ፈክተው የምናያቸውን አበባ ለመቅሰም ይሯሯጣሉ ።ቢራቢሮዎች በየመስኩ ይንሸራሸራሉ ።የመስቀል ወፍና የተለያዩ ወፎችም ከተደበቁበት ጐጆዎቻቸው ይወጣሉ ።በውሃ ሙላት ምክንያት የተራራቀ ዘመድም ይገናኛል ።በአጠቃላይ በመስከረም ስፍራው ሁሉ ለምለም፤ ፍጥረታት ሁሉ ደስታ ያገኛሉ ።በዚህም አዲስ መሆናቸውን አብስረው አዲስ ዓመት በማለት ያከብራሉ ።

እንቁጣጣሽ ማለት ደግሞ የተለያዩ ምክንያቶች ያሉት ስያሜ ነው ።የመጀመሪያው እንቁጣጣሽ ማለት ምድሪቱ በአበባ የምትንቆጠቆጥበት በመሆኑ ማሸብረቅ እንደማለት ነው ይሉታል። አንዳንዶች ደግሞ እንቁጣጣሽ ማለት እጽ አወጣሽ የሚለውን ትርጓሜ ይይዛል ይላሉ ።በምክንያትነት የሚያነሱትም በመስከረም ወር እጽዋትና አዝርዕት ያብባሉና እጽ አበቀልሽ እንደማለት ይወስዱታል። እንቁ የሆኑ አበቦችና እጽዋትን አፈራሽ እንደማለትም ነው። ሌላው እንቁጣሽ ማለት እንቁ እጣ ወጣሽ የሚለውን ይይዛል። ይህ ማለትም በትውፊት የተቀመጠልን ሲሆን፤ የኖህ ልጅ ካም በእጣ አፍሪካ ስለደረሰቺው መልካም ዕድልን መረጥህ እንደማለት እንደሆነም ይነገራል ።ሌላው እንቁ እጣ አመጣሽ የሚለው ሲሆን፤ ንግስት ሳባ ለሰለሞን የሰጠችው ከሀርና እንቁ የተሠራውን ስጦታ ያመለክታል። የመጨረሻው ደግሞ ለሳባ እንቁ ለጣቷ መሰጠትን የሚይዝ ነው።

ቅዱስ ዮሐንስ የሚባለው ደግሞ በነቢዩ ዘካሪያስ ልጅ በመጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ሲሆን፤ መጥምቁ ዮሐንስ በብሉይና ሃዲስ መካከል የተፈጠረ እና «መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ» እያለ ስለ ክርስቶስ አዳኝነት እየመሰከረ በምድረ በዳ የንስሐን ጥምቀት እያጠመቀ የኖረ፣ በመጨረሻም በሄሮድስ ትዕዛዝ ጭንቅላቱን የተቆረጠ ትልቅ ሰማዕት ነው ።በዚህም ምክንያት የቤተክርስቲያን አባቶች የበዓላትን ስርአት ሲሰሩ፣ ይህ በዓል ለመጥምቀ መለኮት ዮሐንስ መታሰቢያ እንዲሆንና በእሱ ስምም እንዲጠራ በመወሰናቸው ነው ።

በመጨረሻ ለምን አውደ ዓመት እያልን እንጠራዋለን የሚለውን እንመልከት ።ዘመናት ዘመንን እየወለዱ ሰዓታት ደቂቃ ወይም ሰከንድን እየሰፈሩ፤ እለታት ሳምንታትን ሳምንታት ወራትን ወራት ደግሞ ዓመታትን እየተኩ አሁን ያለንበትን ጊዜ ይሰጡናል ።በእነዚህ መካከል የሚከወነውን ኡደት ደግሞ የምናየውና የምንገልጸው የዓመቱን ዙረት በማየት ነው ።እናም አውደ ዓመት ማለት የዓመት ዙረት የሚለውን ትርጓሜ ይይዛል ።ለዚህም ነው አውደ ዓመት እያልን እንድናከብር የሆነው ።

ልጆች መስከረም የዘመን መለወጫ ወርም በመባል ይጠራል ።ዘመን መለወጫ የተባለውና ለምን መስከረም ወር ላይ እንደሆነ ሊቃውንት እንዲህ በማለት ያብራሩታል። ብርሃናት/ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት/ የዓመት ዑደታቸውን በጳጉሜ ወር ጨርሰው በመስከረም ወር ስለሚጀምሩ ነው ።ያን ጊዜ ሌሊቱም ከቀኑ ጋር ይተካከላል ።በመሠረቱ ዘመን ተለወጠ ሲባል የሚለወጡት ወራቱ ብቻ አይደሉም ።በወቅቱ የሚከሰቱት/የተከሰቱት/ መልካምም ሆነ ክፉ ነገር ጭምር ነው ።ዘመን መለወጫ ላይ የሰው ልጆች ሕይወትም የሚለወጥበት ጊዜ ነው ።ተማሪው ተምሮ ወደቀጣዩ ክፍል /ደረጃ/ የሚለወጥበት፣ ገበሬው የክረምቱን ወራት በሚገባ ተጠቅሞ የሚቀጥለውን የበጋ ወራት የሚቀበልበት፣ ሠራተኛው የክረምቱን ዝናብ ታግሶ የፀሐይን ወራት የሚያይበት ሌላም ሌላም ክስተቶች የምናይበት ነው ።ስለዚህም እነዚህ ሁሉ ክስተቶችን እያየን ስንሄድ ዘመን ተለወጠ እንላለን ።

ልጆች በአባቶች ምርቃት ልሰናበታችሁ ።ምክንያቱም ይህ ዘመን ሲከበር ምርቃቶች በየአቅጣጫው ይጎርፋሉ። እናም እኔም እንዲህ ልላችሁ ፈለግሁ ።አሜን ማለቱን እንዳትረሱ እሺ «ዝናሙን ዝናመ ምሕረት፣ እህሉን እህለ በረከት ያድርግልን፣ ሰላም ይስጠን፣ እህል ይታፈስ፣ ገበሬ ይረስ፣ አራሽ ገበሬውን፣ ሳቢ በሬውን ይባርክ፣ ቁንጫን፣ አንበጣን፣ ትልን... ያጥፋ፣ ምቀኛን ሸረኛን ያስታግስልን፣ ወጡ ገቡ ሰቡ ረቡ የሚለውን ሁሉ እግሩን ቁጠማ ዓይኑን ጨለማ ያድርገው »። መልካም አዲስ ዓመት!!

# ስፖርት





## የአዲሱ ዓመት የኢትዮጵያ እግር ኳስ አንጸባራቂ ተስፋ

**ቦጋስ አበበ**

በደቡብ አፍሪካ (PSL) ሊግ ሶስት ጨዋታዎችን ተቀይሮ አንድ ጨዋታ ደግሞ ቋሚ ተሰላፊ ሆኖ ወደ ሜዳ በመግባት ለክለቡ ማሚሎዲ ሰንዳውንስ በአራት ጨዋታ ሶስት ግቦችን ያስቆጠረው ወጣት ኢትዮጵያዊ ተጫዋች ባለፉት ሳምንታት የደቡብ አፍሪካ መገናኛ ብዙሃንን ትኩረት ስቧል ። ይህ አንጸባራቂ ወጣት ኮከብ የኢትዮጵያ እግር ኳስ የአዲሱ አመት ትልቅ ተስፋም ነው። ከጉቶ ሜዳ ተነስቶ የአፍሪካ እግር ኳስ የወቅቱ መነጋገሪያ የሆነው አቡበከር ናስር።



የሰንዳወንስ ምክትል አሰልጣኝ ሩላኒ ሞኮዬዋና ሰሞኑን ስለዚህ ተስፈኛ ኮከብ በሰጡት አስተያየት እንዲህ አሉ "በአስደናቂ ተጫዋቾች በመከበቡ በቶሎ ለውጥ ማሳየት ይችላል ። ለሁሉ ነገር አዲስ ተጫዋች ስለሆነ በደቡብ አፍሪካ ውስጥ እንዲረጋጋና ሙሉ ብቃቱን እንዲያሳይ ደጋፊዎች ትእግስተኛ ሆነው መጠባበቅ አለባቸው"። አንዳንድ ዘገባዎች አቡበከር በቋንቋ የተነሳ ችግር ውስጥ መግባቱን ያወሱ ቢሆንም ሰሞኑን የተሰራጩ መረጃዎች ተጫዋቹ ሜዳ ውስጥ ከአሰልጣኞች ጋር እንዲግባባ ክለቡ አስተርጓሚ መመደቡን አትተዋል። እንደ ደቡብ አፍሪካው ኪኮፍ መፅሄት ዘገባ አቡበከር ናስር በቀጣይ ጨዋታዎች በሜዳው ውስጥና ከሜዳ ውጭ መነጋገሪያ ሆኖ ይቀጥላል።

አቡበከር ናስር ለሰንዳውንስ የመጀመሪያውን ጨዋታ ያደረገው በቲ ኤስ ጋላክሲ 1ለ0 በተሸነፈበት ጨዋታ ላይ ነበር ። በጨዋታው ከተቀያሪ ወንበር ላይ ተነስቶ በመግባት ለደቂቃዎች ቢጫወትም ውጤቱን የሚቀይር ብቃት ውስጥ አልነበረም ። በሁለተኛው ጨዋታው አሁንም ተቀይሮ በመግባት ደቂቃዎችን የመጫወት እድል አገኘ ። ሜመሎዲ ሰንዳውንስ ተጋጣሚውን ካይዘር ቺፍን 4ለ0 በሆነ ውጤት ሲያሸንፍ በጨዋታው ምርጥ ብቃቱን በማሳየትና አስደናቂ ግብ ማስቆጠር ችሏል። የደቡብ አፍሪካ ሊግን የሚያደምቅና ወደ አውሮፓ ለመሻገር ተስፋ ያለው ተጫዋች ሆኖ በመጠቀስ የአፍሪካን የስፖርት ሚዲያዎች ማነጋገሩን ቀጥሏል። የሰንዳውንስ አሰልጣኞች ከተለያዩ ሚዲያዎች ጋር ባደረጓቸው ውይይቶች በክለባቸው እንደአቡበከር አይነት አዳዲስ ተጫዋቾች በልምምድና ጨዋታዎች ብቃታቸውን እያሻሻሉ በመሄድ ጥሩ ደረጃ ላይ እንደሚደርሱ እምነት እንዳላቸው ተናግረዋል ። 22ኛ ዓመቱን የያዘው አቡበከር በሰንዳውንስ የቢጫና ሰማያዊ 28 ቁጥር ማሊያ ለብሷል ።

አቡበከር ናስር በደቡብ አፍሪካ ከፍተኛ የክለቦች የሊግ ውድድር በመጫወት 5ኛው ኢትዮጵያዊ ነው ። ከእሱ በፊት ፍቅሩ ተፈራ፤ ጌታነህ ከበደ፤ ፍስሐ ይመር በጋሻውና መሀመድ ኢብራሂም በ6 የተለያዩ ክለቦች መጫወት ችለዋል። በተለይ ፍቅሩ ተፈራ በሁለቱ ታላላቅ ክለቦች ኦርላንዶ ፓይሬትስና ሱፐር ስፖርት ዩናይትድ ከመጫወቱም በላይ ለሁለት ጊዜያት የደቡብ አፍሪካ ሊግን በማሸነፍ ከፍተኛውን ውጤት ያስመዘገበ ነው ። ጌታነህ ከበደ ደግሞ በቢድቬስት ዌስትና በፕሪቶሪያ ዩኒቨርሲቲ 19 ጨዋታዎችን በማድረግ በደቡብ አፍሪካው ሊግ 6 ጎሎችን በስሙ አስመዝግቧል ። አቡበከር ከነዚህም ተጫዋቾች የተሻለ ጅማሬ ያሳየ ባለ ተሰጥኦ ወጣት መሆኑን ተከትሎ በርካቶች ከፍ ላለ ስኬት ከወዲሁ አጭተውታል።

አቡበከር ናስር ወደ ደቡብ አፍሪካ ከመሻገሩ በፊት በኢትዮጵያ ቡና የስፖርት ክለብ እኤአ እስከ 2025 የሚቆይበት የኮንትራት ውል ነበረው ። ሰንዳውንስ ሊያዛውረው ከፈለገ በኋላ በውሰት ለሌላ ክለብ በመስጠት ሊያጫውተው አስቦ ነበር ። ስለዚህም ለስድስት ወራት በቡና ስፖርት ክለብ ውስጥ ቆይታ አድርጓል ። የእንግሊዘኛ ቋንቋውንም በዚህ ወቅት ለማሻሻል አስተማሪ ተቀጥሮለት ሁሉ ተሰርቷል። በመጨረሻም ቡና የስፖርት ክለብ በፕሮቶሪያ ለሚያደርገው ቆይታ ወጪውን ከሸፈነለት በኋላ ለሁለት ሳምንታት የሰንዳውንስ ቆይታ አድርጎ በ250ሺ ዩሮ የዝውውር ሂሳብ ለደቡብ አፍሪካው ክለብ ሙሉ በሙሉ ሊፈርም ችሏል ። ከሰንዳውንስ ባሻገር ካይዘር ቺፍ የሚፈልገው ሌላው የደቡብ አፍሪካ ክለብ ነበር ። ኪክአፍ መፅሄት እንደዘገበው የደቡብ አፍሪካ ክለቦች ሽሚያ ውስጥ ከመግባታቸው በፊት በአልጄሪያና በግብፅ ክለቦች ይፈለግ ነበር። የጆርጅያ ክለብ እና በስፔን ዝቅተኛ ዲዚዮን ያሉ ክለቦች ሊወስዱት ሙከራ እንዳደረጉም አውስቷል ።

አቡበከር ወደ ደቡብ አፍሪካው ክለብ ከመዛወሩ በፊት ከ2014 እስከ 2016 እኤአ በሃረር ከተማ በመጫወት የክለብ ሕይወቱን ጀምሯል ። ከ2016 ጀምሮ ደግሞ ለስድስት ዓመታት በኢትዮጵያ ቡና ስፖርት ክለብ በመጫወት አሳልፏል ። በቡና ቢ ቡድን መጫወት ከጀመረ በኋላ በአጭር ጊዜ ውስጥ ዋና ቡድን ተቀላቅሏል ። ከ23 በላይ የፕሪሚዬር ሊግ ጨዋታዎችን በማድረግ 29 ጎሎችን በስሙ አስመዝግቧል ። በ2021 የኢትዮጵያ ፕሪሚዬር ሊግ ኮከብ ግብ አግቢ ሆኖ በ24 ጎሎች ያሸነፈ ሲሆን ሌሎች የምርጥ ተጨዋች ሽልማቶችንም ተቀዳጅቷል ።

አቡበከር ናስር ባለፉት 3 ዓመታት በዓለም ዋንጫ፤ በአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያዎች፤ በወዳጅነት ጨዋታዎች፤ ዋና ውድድሮች ለብሔራዊ ቡድን 21 ጨዋታዎችን አድርጓል ። 5 ጎሎችንም ከመረብ አሳርፏል። በብሔራዊ ቡድን ማሊያ ካገባቸው ጎሎች ሁለቱም በወዳጅነት ጨዋታዎች ላይ ያስቆጠራቸው ሲሆኑ በባህርዳር ስታድዮም በኡጋንዳና በማላዊ ላይ ነው ። ሌሎች ሁለት ጎሎችን ደግሞ በአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ በባህርዳር ስታድዬም በማዳጋስካር ላይ እንዲሁም በዓለም ዋንጫ ማጣሪያ ዚምባቡዌ ላይ በሃራሬ ስታዲዬም አስቆጥሯል ።

የደቡብ አፍሪካው ክለብ ሜመሎዲ ሰንዳውንስ በአገሪቱ ከፍተኛ የክለቦች ውድድር ከ15 ጊዜያት በላይ ዋንጫዎችን አሸንፏል ። የአፍሪካ ቻምፒዮንስ ሊግና የአፍሪካ ሱፐር ካፕንም ያሸነፈ ምርጥ ፕሮፌሽናል ክለብም ነው ። ሜመሎዲ ሰንደውንስ በደቡብ አፍሪካ እግር ኳስ በ11 ሚሊዮን ዶላር የዋጋ ተመን ሃብታሙ ክለብ ሲሆን፤ ዋና ባለቤቱ ፓትሪስ ሞትሶፔ ታዋቂ የደቡብ አፍሪካ ቢሊዬነርና የማዕድን ኢንቨስተር ናቸው። መቀመጫውን በፕሪቶሪያ፤ ቲስዋኔ ያደረገው ክለቡ ከተመሰረተ 52 ዓመታትን አስቆጥሯል ። በሰንዳውንስ የ46 ተጨዋቾች ስብስብ አብዛኛዎቹ ደቡብ አፍሪካዊ ቢሆኑም ከምስራቅ አፍሪካና ከደቡብ አሜሪካ ጭምር ፕሮፌሽናሎች ተሰባስበዋል። ከኢትዮጵያ፤ ኬንያ ፤ ኡጋንዳ፤ ኡራጋይ፤ ቺሊና ቦሎቪያ የመረጡ ተጨዋቾች በቡድኑ ይገኛሉ ። ከነዚህ ሁሉ ልቆ ግን አቡበከር በክለቡ ደጋፊዎች የተወደደ ይመስላል።